የጌታ ጸሎት

በቶም ዎከር



በአስራዎቹ ዕድሜ ለሚገኙ ታዳጊዎች የተዘጋጁ አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች

ከ100-107 ባሉ አጫጭር የካቴኪዝም ጥያቄዎች ላይ የተመረቱ

ክፍል IX

ሁሉም ጥቅሶች ከ1962 ዓ.ም

የአማርኛ ትርጉም መጽሐፍ

ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

የቅጂ መብት © 2017 በ

Children's Ministry International, Inc.

2331 4th St., Suite 106, Tucker, GA 30084-4499 E-mail፡
childrensministry1@earthlink.net Internet፡ childministry.com

ስልክ: (770) 493-8952

ማውጫ

መቅድም ለአስተማሪዎች 4
ምዕራፍ 1 የእግዚአብሔር ቀረቤታ እና ክብር 5
ምዕራፍ 2 የእግዚአብሄር መንግስትና ፈቃድ 5
ምዕራፍ 3 የእግዚአብሄር አቅርቦትና ምህረት 5
ምዕራፍ 4 የእግዚአብሄር ማዳንና ልቀት 5
ተጨማሪ መግለጫ 5
የታዳጊዎች የስራ ሉኮች 5

መቅድም ለአስተማሪዎች

እግዚአብሔር የማይሞቱ ነፍሳትን ለእግዚአብሔር አገልግሎት እና ክብር የማሰልጠን አስደናቂ ኃላፊነት ሰጥቶሃል። የታዳጊዎቹ ዘላለማዊ ድነት እና ምድራዊ ደህንነት ሀላፊነትህን በታማኝነት መወጣት አለመወጣትህ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል። ያንተ ጥንቃቄ የተሞላበት ሃይማኖታዊ መመሪያ ነፍሳቸውን ሊመግብ እና የሕያውና እውነተኛውን አምላክ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዓመታት እንዲያገለግሉ ሊያስታጥቅ ይችላል።

ይህንን አስፈላጊ ተግባር የእምነት እና የፍቅር ስራ አድርገህ ያዘው። ለእያንዳንዱ ምዕራፍ በምታደርገው ዝግጁት ትልቅ ትጋት አሳይ፣ ደግሞም ጸልይ። በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጆች እነዚህን ትምህርቶች በቀላሉ እንዲያስታወሷቸው ከማድረግ ወይም መልሶችን ብቻ ከማስተማር ይልቅ በልባቸው በመረዳት የመተግበር አስፈላጊነትን አስጨብጣቸው። ካቴኪዝምን ማጥናት እና የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀታቸውን ማሳደግ በአሁኑ ዕድሜያቸውና በሕይወታቸው ሙሉ እንዴት እንደሚጠብቃቸው፣ እንደሚያጠናክራቸው እና እንደሚያበረታታቸው አጽንኦት ሰጥተህ ንገራቸው።

በእምነትና በጸሎት ከድካምህ ብዙ ፍሬ ታያለህ። ልጆቹም ተነሥተው ያመሰግኑሃል። (ምሳ 31፡28)። በእውነት፣ ለመንግሥቱ ለሚደረግ ለዚህ ጠቃሚ ጥረትህ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክህ!

<u>የዌስትሚኒስተር ካቴኪዝም በአጭሩ</u>

በ1643 የእንግሊዝ ፓርላማ ጥልቅ የሆነ ነገር አደረገ። 121 ፓስተሮች እና 30 ምእመናን ያቀፈ ጉባኤ ጠራ፤ ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ በዓለም ላይ የሚታወቁ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያላቸው የሃይማኖት ሊቃውንት ነበሩ። እነዚህ ለቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫ እና የአስተዳደር መዋቅር ለመቅረጽ ተሰበሰቡ፣ ያደረጉትም ጥረት በመጨረሻ የአምልኮ ማውጫ፣ የእምነት ኑዛዜ እና ሁለት ካቴኪዝም አንዱ ትልቅ የካቴኪዝም ጥልቅ ጥናት እና አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማስተማር የሚያገለግል አጭር ካቴኪዝምን አስገኘ። ለብዙ አመታት ያደረጓቸው በርካታ ስብሰባዎች የዌስትሚኒስተር ጉባኤዎች በመባል ይታወቁ ነበር።

በእግዚአብሔር መሰጠት ውስጥ፣ ካቴኪዝም እንደ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ፍቺዎች ጠቃሚ ሆነው ይቆያሉ። ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ዘመናዊቷ ቤተ ክርስቲያን በካቴኪዝም ውስጥ ለተጠቃለለው ጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ብዙ ጊዜ ትኩረት አትሰጥም። በተለይ ታዳጊ ወጣቶች ለሕይወት እና ለተግባር የሚሆን ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ሳያገኙ ሲቀሩ በጣም ይሠቃያሉ። አብያተ ክርስቲያናት፣

የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች እና ወላጆች በአደራ በተሰጣቸው ታዳጊ ወጣቶች ውስጥ ይህን መሠረት እንዲያሳድጉ ለማበረታታት፣ ቻይልድ ሚኒስቴር ኢንተርናሽናል (ሲኤምአይ) ለአጭር የካቴኪዝም ትምህርት ምቹ ህኔታ የሚፈጥርና የሚደግፉ ቁሳቁሶችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫልም።

<u>ተከታታይ አደረጃጀት</u>

“በአስራዎቹ ዕድሜ ካሉት ታዳጊዎች እስከ ወጣቶች” ተከታታይ ዘጠኝ ክፍሎችን (ወይም መጽሃፎችን) ያቀፈ ነው፡

ክፍል I እግዚአብሔር ለሰው ያለው ራዕይ

ክፍል II እግዚአብሔር ለአለም ያለው እቅድ

ክፍል III የሰው ልጅ ኃጢአት እና ውድቀት

ክፍል IV ለኃጢአተኞች የእግዚአብሔር መፍትሄ

ክፍል V የእግዚአብሔር አስደናቂ ጸጋ

ክፍል VI ለእግዚአብሔር ያለብን ግዴታ

ክፍል VII ለሌሎች ያለብን ግዴታ

ክፍል VIII የእግዚአብሔር የጸጋ መንገድ

ክፍል IX የጌታ ጸሎት

እያንዳንዱ ክፍል ከሶስት እስከ ስምንት ምዕራፎች አሉት።. እንዲሁም እያንዳንዱ ምዕራፍ ሦስት ክፍሎችን ማለትም ካቴኪዝም፣ የቃል ጥቅስና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያቀፈ ነው። የመጨረሻዎቹ ሁለት ክፍሎች የካቴኪዝሙን ክፍል ይደግፋሉ፤ ትምህርቱንም ይጠቁማሉ። የቃል ጥቅሱን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ስታስተምር፣ ካቴኪዝም እና ቅዱሳት መጻህፍት በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ልጆች ለሚገጥሟቸው ችግሮች እና ተግዳሮቶች አስፈላጊ መሆናቸውን አጽንኦት ስጥ።

<u>ሃሳቦችን እና ምክሮችን ማስተማር</u>

ከማስተማርህ በፊት, ሙሉውን ምዕራፍ በጥንቃቄ አጥና። ግልጽ የሆነ አጠቃላይ እይታ ለማግኘት የተዘረዘረውን የመማር ዓላማ እና ካቴኪዝምን ተጠቀም። ትምህርትህን

ጤናማ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ የተመሠተ አድርግ። እንዲሁም ሌሎች ክፍሎች እና ምዕራፎች ሊሸፍኗቸው ወደ ሚችሉት ርእሶች በጣም ርቀህ እንዳትሄድ ተጠንቀቅ።

የመማሪያው ዓላማ በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ይታያል። ትምህርቱን በችኮላ በማለፍ ወይም የራስ የመተዳደሪያ መርሃ ግብር ለማክበር ሲባል ይህንን አላማ መስዋት የማድረግ ፈተናን ተቃወም። በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የተገለጹትን ዓላማዎች ሳያሳኩ ትምህርቱን በመቸኮል ከማለፍ ይልቅ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ላይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ክፍለ ጊዜዎችን ማሳለፍ የተሻለ ነው።

ታዳጊዎች በአንዳንድ የካቴኪዝም ጥያቄዎች እና መልሶች ውስጥ ያሉትን የቃላት እና የአረፍተ ነገር አወቃቀሮችን ለመረዳት ትንሽ አስቸጋሪ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ያልተለመዱ ቃላትን መፈለግ እና ካቴኪዝምን በራሳቸው ቃላቶች እንደገና መፃፍ ግንዛቤን ይጨምራል። ምንም እንኳን ካቴኪዝምን ማስታወስ ትልቅ ጥቅም ቢሰጥም፣ ትርጉሙን ግልፅ ቀጥተኛ በሆነ ቋንቋ ማብራራት የበለጠ አስፈላጊ ነው። በእርግጥም ያልተረዱትን ቃላት ማስታወስ የመንፈሳዊ እድገትን አቅምን ይገድባል። መረዳቱ ሳይረዱት በቃል መሸምደድን ያስከትላል።

የውይይት ጥያቄዎች ምልክት በተደረገባቸው መልሶች ተደግፈው በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ባሉት ሦስት ክፍሎች ውስጥ ይገኛሉ። ሁሉንም መልስ ያላካተቱ፤ የመወያያ ጥያቄዎች በአባሪው ታገኛቸዋለህ። እነዚህን ጥያቄዎች ገልብጠህ ለተማሪዎችህ ማሰራጨት አለብህ። እነዚህ ጥያቄዎች ታዳጊዎች የእያንዳንዱን ምዕራፍ የመማር አላማ ማሳካት መቻላቸውን ለመወሰን በጣም አስፈላጊ ናቸው። እነዚህን ጥያቄዎች በተለያዩ መንገዶች ልትጠቀምባቸው ትችላለህ፣ ግን አንዱ አማራጭ እያንዳንዱን ክፍል ካስተማርክ በኋላ ወዲያውኑ በክፍል ውስጥ ማወያየት ነው። በማናቸውም የተሳሳቱ ወይም ያልተሟሉ ምላሾች ታዳጊዎቹን እርዳቸው።

የዝማሬዎች ዝርዝር በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ተቀምጠዋል። ለመጨረሻ ጊዜ ዋና ዋና ነጥቦቹን ለማጉላት አንድ ወይም ከዚያ በላይ መዝሙሮችን ዘምሩ ወይም ደግሞ እንደ የመደምደሚያ ጸሎት ከመዝሙር አንዱን ጮክ ብለው ያንብቡ። የሥላሴ መዝሙር (1990) አብዛኛዎቹን እነዚህን የተመረጡ መዝሙሮች አካቶ ይዟል።

በመጨረሻም፣ ትምርትህን ለማጠናከር እና የታዳጊዎችን ትምህርት ለማሻሻል በሲኤምይ(CMI)-የተዘጋጁ የፓወር ፖይንት ስላይዶችን መጠቀም አለብህ። ለእያንዳንዱ ክፍልና ምዕራፍ የሚሆኑ የፓወር ፖይንት ማቅረቢያዎች ማግኘት ትችላለህ። ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ የተለዩ የማስተማሪያ ማስታወሻዎች በፓወር ፖይንት ይሰጣሉ።

ለተጨማሪ መረጃ ምንጮች

Palmer, Edwin H. The Five Points of Calvinism. Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1999. Vincent, Thomas. The Shorter Catechism Explained from Scripture. Carlisle, PA: Banner of Truth Trust, 2010.

Vos, Johannes G. The Westminster Larger Catechism: A Commentary. Edited by G. I. Williamson Phillipsburg, NJ: Presbyterian and Reformed Publishing Company, 2002.

ክፈል IX
የጌታ ጸሎት

ምዕራፍ 1

የእግዚአብሔር ቀረቤታ እና ክብር

ዓላማ በአክብሮት መጸለይ፣ እንደ ልጆቹ ወደ አብ መምጣት እና ክብሩን መፈለግ

1 ካቴኪዝም* ጥ. የጌታ ጸሎት መቅድም ምን ያስተምረናል?

መ. የጌታ ጸሎት መቅድም፣ እርሱም፣ በሰማያት የምትኖር አባታችን፣ እኛን ለመርዳት የሚችል እና ዝግጁ የሆነ አባት፣ ልጆች እንደመሆናችን መጠን በፍጹም አክብሮትና እምነት ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ያስተምረናል። እና ከሌሎች ጋር እና ለሌሎች መጸለይ አለብን.

ጥ. በመጀመሪያው ልመና ውስጥ ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. በመጀመሪያው ልመና ማለትም፣ ስምህ ይቀደስ በሚለው፣ እግዚአብሔር እኛን እና ሌሎች እራሱን በሚገልጥበት ነገር ሁሉ እንድናከብረው እንጸልያለን። እና ሁሉንም ነገር ለራሱ ክብር እንደሚሰጥ።

የማስታወሻ ጥቅስ፡- ዕብራውያን 4፡16 “እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፡- <u>የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ</u>

ዓላማ

በአክብሮት መጸለይ፣ እንደ ልጆቹ ወደ አብ መምጣት እና ክብሩን መፈለግ

ካቴኪዝም

ጥ. የጌታ ጸሎት መቅድም ምን ያስተምረናል?

መ. በሰማያት የምትኖር አባታችን የሚለው የጌታ ጸሎት መቅድም እኛን ለመርዳት የሚችል እና ዝግጁ የሆነ አባት ልጆች እንደመሆናችን መጠን በፍጹም አክብሮትና እምነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ከሌሎች ጋር እና ለሌሎች መጸለይ እንዳለብን ያስተምረናል።

ጥ. በመጀመሪያው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. በመጀመሪያው ልመና ማለትም፣ ስምህ ይቀደስ በሚለው እግዚአብሔር ለእኛና ለሌሎች እራሱን በሚገልጥበት ነገር ሁሉ እንድናከብረውና ሁሉንም ነገር ለእርሱ ክብር እንዲሆን እንጸልያለን።

መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ታዳጊዎች እነዚህን ቃላት እንዲፈልጉ ጠይቃቸው፡ መቅድም፣ አክብሮት፣ ልመና እና የተቀደሰ። የእያንዳንዱን ፍች እንዲያነቡ እና ከዚያም የተጻፈውን ፍቺ ሳያዩ ቃሉን በራሳቸው አባባል ለመተርጎም ይሞክሩ። እያንዳንዱን ቃል በደንብ እስኪረዱት ድረስ ትርጉሙን በማንበብ እና በራሳቸው አባባል በየተራ እንዲገልጹ ንገራቸው። የተጻፈውን ፍች በእያንዳንዱ ጊዜ በቀላሉ የሚደጋግሙ ከሆነ በመጀመሪያ የሁሉንም ቃላት ፍችዎች እንዲያነቡ ምራቸው፤ ከዚያም ሳያዩ የሁሉንም ቃላት ፍች በራሳቸው አባባል ይግለጹ። በመቀጠል፣ የካቴኪዝም ጥያቄዎችን እና መልሶችን እንደገና ካነበቡ በኋላ፣ ስለ መቅድም እና የመጀመሪያ ልመና የቻሉትን ያህል በራሳቸው አባባል እንዲያብራሩ ጠይቃቸው።

ከዚያም ታዳጊዎች የቃላቶቹን በተሻለ ሁኔታ በመረዳት በማብራራት ከላይ ያሉትን ሁለቱን የካቴኪዝም ጥያቄዎች እና መልሶች በራሳቸው አባባል እንዲጽፉ አስተምቸው። ከዚህ በታች እንደገና ለመሣፍ የተሞከረው ምሳሌ ነገሩ ምን ሊመስል እንደሚችል ያሳያል።

ጥ፡ "በሰማያት የምትኖር አባታችን" ከሚለው የጌታ ጸሎት መቅድም ምን ተማራችሁ?

መ. ወደ ምድራዊ አባትህ በአክብሮት እና በልበ ሙሉነት እንደምትመጣ ሁሉ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሁ መቅረብን ትማራለህ። አባታችን በሚለው ውስጥ ያለው "የእኛ"

የሚለው ተውላጠ ስም ደግሞ ጸሎት ከሌሎች ጋር እና ለሌሎች መሆን እንዳለበት ያመለክታል።

ጥ፡- “ስምህ ይቀደስ” በሚለው የመጀመሪያ ልመና ስለ ምን ትጸልያለህ?

መ. እግዚአብሔርን ለማክበር እና እግዚአብሔር ክብሩን በሁሉም ነገር እንዲያሳይ ትጠይቃለህ።

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ</u>

ታዳጊዎች እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚደግፉ የካቴኪዝም ሀረግ(ጎች) እንዲለዩ ጠይቃቸው፣

መዝሙር 72፡19ን “የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘላለም ይባረክ፤ ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይምላ። ይሁን፤ ይሁን።”

ራሱን በሚገልጸበት ነገር ሁሉ እርሱ ይወደስ ዘንድ ነው።

የሐዋርያት ሥራ 12:5፣ “ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።”

ከሌሎች ጋር እና ለሌሎች መጸለይ አለብን

ሮሜ 8፡15 “አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና።”

እንደ ልጆች ሁሉ በድፍረት ወደ እግዚአብሔር አባት ቅረቡ

ሮሜ 11፡36 “ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና። ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን! አሜን።

ራሱን በሚገልጸበት ነገር ሁሉ እርሱ ይወደስ ዘንድ ነው።

ኤፌሶን 3፡12፣ “በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን።”

በፍጹም እምነት ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ

ያዕቆብ 4:8 "ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል"

በፍጹም እምነት ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ

1ኛ የዮሐንስ መልእክት 3፡1 “እግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ! እንዲሁም ነን።”

እንደ ልጆች ወደ አባታችሁ እግዚአብሔር ቅረቡ

<u>የካቴኪዝም ጥያቄዎች</u>

1. መቅድም ምንድን ነው?

ሰዋናው ጽሑፍ በፊት የሚቀድም ወይም የሚመጣ መግቢያ ነው። በጸሎት ረገድ፣ መቅድም የሚያተኩረው አእምሮ ላይ ነው። ስለዚህ አማኞች ልመናቸውን ከማቅረባቸው በፊት ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

2. በምትጸልይበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለብህ በምን ዓይነት አመለካከት ወይም እይታ ነው?

ሁሉን ቻይ አምላክ ሊረዳችሁ እንደሚፈልግ አውቃችሁ ልጆች ወደ ምድራዊ አባቶቻቸው እንደሚቀርቡት በቅዱስ አክብሮት እና በራስ መተማመን ወደ አብ መቅረብ አለብን።

3. በጌታ ጸሎት ውስጥ ከሌሎች ጋር እንድትጸልይ የሚያስተምርህ የትኛው የተውላጠስም ገላጭ ነው?

አባታችን በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው “የእኛ” የሚል ተውላጥስም ከሌሎች ሰዎች ጋር አንድ ላይ መጸለይን ያመለክታል። አብረው በመጸለይ አንዳቸው ለሌላው ልመና እንደሚቀርቡ አጥብቆ ይጠቁማል፣ ስለዚህ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ምሳሌዎችን ይሰጣሉ። እርግጥ ነው የጌታ ጸሎት ሁልጊዜ ጸሎት ቢያንስ ከአንድ ሰው ጋር መከናወን እንዳለበት አያመለክትም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናየው ብዙ ጊዜ ኢየሱስ እንዲሁም ብዙ ቅዱሳን ብቻቸውን ይጸልዩ ነበር። ይሁን እንጂ “የእኛ” የሚለውን መጠቀሙ ጸሎት ከሌሎች ጋር መሆን እንዳለበት ያስተምረናል። እንዲሁም የልመና ጸሎት የሚጸልየው ሰው ፍላጎቶችን ብቻ የሚመለከቱ መሆን የለባቸውም።

4. በመቅድሙ እግዚአብሔርን እንድናወድስ የሚያስታውስ የትኛው ክፍል ነው?

“በሰማያት የምትኖር” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር በቅድስና እና በበጎነት ከእኛ እጅግ ልቆ በሰማያት የሚኖር መሆኑንና ያሳስበናል።

5. በመቅድሙ እግዚአብሔር በሰማይ ቢሆንም በጸሎት ወደ እርሱ መቅረብ እንደምንችል የሚያስታውስ የትኛው ክፍል ነው?

“አባታችን” የሚለው እግዚአብሔር በክርስቶስ የማዳን ሥራ እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ እንደተቀበለን ያስታውሰናል። (ክፍል V፣ ምዕራፍ 4)።

6. በዮሐንስ 1፡12 በመሰረት እውነተኛና ሕያው የሆነውን ብቸኛ አምላክ አባታችን ብሎ የመጥራት መብት ያለው ማን ነው?

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ብቻ በእምነት እና በንስሃ እግዚአብሔርን አባታችን ብለው መጥራት ይችላሉ። (ክፍል VIII፣ ምዕራፍ 3)። "ለተቀበሉት ሁሉ ግን (ኢየሱስን) በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" (ዮሐንስ 1፡12)።

7. አጭሩ ካቴኪዝም ቁጥር 1 "የሰው ልጅ ትልቁ ፍጻሜው እግዚአብሔርን ማክበር ነው" ይላል። አጭር ካቴኪዝም ቁጥር 101 እንደሚያብራራው ይህ መግለጫ ከመጀመሪያው የጌታ ጸሎት ልመና ጋር እንዴት ይዛመዳል?

ካቴኪዝም #101 ጸሎት እግዚአብሔርን ለማክበር አንዱ መንገድ እንደሆነ ይገልጣል። ይህም የሰው ዋና ፍጻሜ ነው። አማኞች በቅንነት “ስምህ ይቀደስ” ብለው ሲጸልዩ፣ ራሱን በሚገልጸበት ነገር ሁሉ እርሱን እንዲያከብሩ ይጠይቃሉ።

<u>የቃል ጥቅስ</u>

ዕብራውያን 4፡16 “እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።

አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት ከእግዚአብሔር ጋር በነበራቸው የጠበቀ ኅብረት ደስተኞች ነበሩ። እባቡ ግን ሔዋንን ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ እንዳትታዘዝ ፈተናት። እርስዋም ፈቃዷን ሰጠችው፣ አዳምም ወዲያው ተከተላት። (ዘፍ 3፡1-6)። ይህ የመጀመሪያ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ለያቸው፤ ይህ የሰው ልጆችን ሁሉ ወደ ጨለማ የክፋትና የመከራ ዘመን ውስጥ አስገባቸው። (ክፍል III፣ ምዕራፍ 1 እና 2)። የተወሰነ ጣልቃ ገብነት ባይኖር፣ መላው የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር ያለውን ግንኙነት እንደገና ለመመሥረት ፈቃደኛ ባልሆነ ነበር። የእግዚአብሔር ጸጋ ከሌለ ማንም ሰው ይቅርታን፣ ድጋፍን፣ ምክርን፣ ጥንካሬን፣ መመሪያን፣ ጥበቃን ወይም የምግብ አቅርቦት ለማግኘት በእሱ እርዳታ ሊተማመን አይችልም።

የቃል ጥቅሱ ንጉሱን የሚሰሙትን ብቻ እንጂ ሁሉም የሰው ልጆች ወደ መንግሥተ ሰማያት የዙፋን ክፍል እንደሚገቡ የሚያመላክት አይደለም። “የጌታን ስም የሚጠራ…” (ሮሜ 10፡13)፣ “በጸጋው…በእምነት አድኗቹሀልና” (ኤፌሶን 2፡8) እንዲመጡ ይጋብዛል። በአጭሩ፣

የእግዚአብሔር አስደናቂ ጸጋ (ክፍል V) የሚቀበሉ ብቻ ንጉሱ እንደሚሰማቸው አውቀው ልመናዎችን ያመጣሉ። የሚጸልዩ ቅዱሳን ብቻ በጸጋው ዙፋን ላይ እርዳታ ሊጠብቁ ይችላሉ።

ተመራጮች በጸሎት መግቢያ በኩል ልመናዎችን ይዘው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን 24/7 መድረስ ይችላሉ። የመግቢያው መንገድ ግን ምላሹን ሊወስን ይችላል። ለስሙ ተገቢውን ክብር ካላመጣችሁ ወደ ጌታ መገኘት በፍጹም አትገቡም። በሲና ተራራ ፊት እንደነበሩት እስራኤላውያን በፍርሃት አትሸበሩ። (ዘጸአት 20፡18-19)። በምትኩ "በቅዱስ አክብሮት እና እምነት" ጸልዩ (አጭር ካቴኪዝም #100)። አናንተን ከኃጢአትና ከመከራ ለማዳን አንድያ ልጁን እስኪሠዋ ድረስ ወደሚወዳችሁ አብ በድፍረት ቅረቡ። (ዮሐ. 3፡16)። አስታራቂ ሆኖ የሚሰራውን ታላቁን ሊቀ ካህናት ክርስቶስን በማወቅ በድፍረት ቅረቡ። ስለ እናንተ ሊማልድ በአብ ቀኝ ተቀምጧልና (ዕብ 1፡3)። አብ ልመናችሁን ከሰማ በኋላ ሁል ጊዜ በሕይወታችሁ ሁሉን ነገር ለበጎ እንደሚያደርግላችሁ በመተማመን በድፍረት ቅረቡ። (ሮሜ 8፡28)።

<u>የቃል ጥቅስ ጥያቄዎች</u>

1. "እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ጸንተን ሀይማኖታችንን እንጠብቅ" (ዕብ. 4፡14) በዚህ ጥቅስ መሰረት በቃል ጥቅስ ውስጥ ያሉት "እኛ" እና "የእኛ" የተባሉት እነማን ናቸው?

   በማስታወሻ ጥቅስ ላይ "በመታመን ወደ ጸጋው ዙፋን መቅረብ" የሚችሉት "ታላቅ ሊቀ ካህናት ...፣ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ" ካላቸው እና "እምነታቸውን አጥብቀው ከሚይዙት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። " ይሽውም የቃል ጥቅሱ አማኞችን ብቻ ወደ ጸጋው ዙፋን ይጋብዛል።

2. ጓደኛህ "ከባድ ችግር ውስጥ ከገባሁ በሰማይ ላለ ትልቅ ሰው እጸልያለሁ፤ እሱም አንዳንድ ጊዜ ይረዳኛል" ይላል እንበል። ይህ አባባል ከጌታ ጸሎት ጋር ይዛመዳል?

   አንዳንድ ሰዎች ከሞላ ጎደል በግድየለሽነት ዝንባሌ ወደ እግዚአብሔርንና ጸሎትን የተላመዱ ይመስላል። ሆኖም፣ የጌታ ጸሎት ስለጸሎት ያስተምራል፤ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው እናም ወደእርሱ በአክብሮታዊ ፍርሃት መቅረብ አለበት።

3. በምትጸልይበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለብህ በምን ዓይነት ዝንባሌ ነው?

   በብዙ መንገድ መልስ የሚሰጥ ቢሆንም፣ የቃል ጥቅሱ በልበ ሙሉነት ስለመጸለይ ይናገራል።

4. "በልበ ሙሉነት" መጸለይ ሲባል ምን ማለት ነው?

እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የምትለምነውን ሁሉ ይሰጥሃል ማለት አይደለም። ይልቁንም፣ እንደ አማኝ እግዚአብሔር እንደሚወዳችሁ፣ ስትጸልዩ እግዚአብሔር እንደሚሰማችሁ፣ ኢየሱስ ስለእናንተ በአብ ፊት እንደሚማልድላችሁ፣ እና እግዚአብሔር በህይወታችሁ ውስጥ ነገሮችን ለበጎ እንደሚሰራ በርሱ መታመን አለባችሁ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፦ የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ

የመጀመሪያው ልመና "ስምህ ይቀደስ" የሚል ነው። ያን ሰው ቅዱስ ነው ብለህ ስታከብረው ሰውን ትቀድሳለህ። እግዚአብሔርን መቀደስ ማለት ማክበር፣ ከፍ ከፍ መድረግ፣ ማመስገን፣ መፍራት፣ ፣ ማምለክ እና ፍጹም፣ ጻድቅ፣ ንጹህ እና ጥሩ በመሆኑ ከፍ ከፍ ማድረግ ማለት ነው። ነገር ግን በመጀመሪያው ልመና የሚቀድሰው እግዚአብሔር ሳይሆን ስሙ ነው ብላችሁ ትቃወሙ ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ስም ዝም ብሎ የሰው ልጅ እሱን የሚጠራበት መጠሪያ ወይም የማዕረግ ስም ብቻ አይደለም። ምንም እንኳ እነዚህ ብዙ ነገር የሚገልጹ ቢሆኑም። የእግዚአብሔር ስም ደግሞ የሚያመለክተው (ሀ) ባህሪውን፣ መለዮውን/attributes፣ ወይም እሱነቱን እና (ለ) ስራዎቹን፣ በተለይም የፍጥረትን መግቦት እና መቤገርትን ነው። የእግዚአብሔር ስም "እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጽበትን ሁሉ" ያጠቃልላል። (አጭር ካቴኪዝም #101)። ስለዚህ፣ የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ ማለት ሰውነቱን ማክበር እና ፍጹም ጻድቅ፣ ቅዱስ፣ ንፁህ እና ጥሩ ሆኖ ይሰራል ማለት ነው።

የመጀመሪያውን ልመና የሚያነቡ ክርስቲያኖች እነርሱ እና ሌሎች ቅዱሳን የጌታን ስም የተቀደሰ እንዲሆን ይጸልያሉ። "እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት፥ በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ።" (መዝሙረ ዳዊት 34፡3) "በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ። በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን።" (1ኛ ዜና 16፡28-29)።

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስም የሚያከብሩ ቅዱሳን ብቻ አይደሉም። መላእክትና ሁሉም ቅዱሳን ጌታን ያከበራሉ። የእግዚአብሔር ዙፋን የእግዚአብሔርን ስም በሚቀድሱ የሰማይ ሰራዊትን ይገልጣል። እና ከዚህ በታች ያሉ ቅዱሳን የሚያደርጉትን ጥረት ይህን ያሳያል። "[ሐዋርያው ዮሐንስ] በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ። በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ።" (ራእይ 5:13) "መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ።አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ።" (ራእይ 7:11-12) "ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው?

አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።" (ራዕይ 15፡4)።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጥያቄዎች</u>

1. "ቅዱስ" ማለት ምን ማለት ነው?

   ሰውን መቀደስ ማለት ቅዱስ አድርገህ በመቁጠር አክብረኸው ማለት ነው።

2. "ክብር" ለሚለው አንዳንድ ተመሳሳይ ትርጉሞች ምንድን ናቸው?

   ክብር መስጠት፡ ማመስገን፡ ውዳሴ መስጠት፡ ማምለክ ክፍ ክፍ ማድረግ ናቸው።

3. "ቅዱስ" ለሚለው አንዳንድ ተመሳሳይ ትርጉሞች ምንድን ናቸው?

   በብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ "ቅዱስ" ማለት የተለየ ማለት ነው። በሚቀራረብ አውድ፡- ጻድቅ፣ ፍጹም፣ ንጹሕ እና ጥሩ ማለት ነው።

4. "ስምህ" የሚለው ምንን ያመለክታል?

   የእሱ ስም ትክክለኛ ስሙን (ለምሳሌ፣እግዚአብሔር)፣ ማዕረጉን (ለምሳሌ፣ የነገሥታት ንጉሥ)፣ ባህሪውን (ለምሳሌ፣ በሁሉም ቦታ መገኘት) እና ሥራውን (ለምሳሌ፣ መቤዠት) ያካትታል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ስም እርሱ ያለውንና የሚያደርገውን ሁሉ ያመለክታል።

5. የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ ሲባል ምን ማለት ነው?

   ማንነቱን ማክበር እና ፍጹም ቅዱስ ሆኖ ይሰራል ማለት ነው።

6. *አቤቱ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፥ እንደ ሥራህም ያለ የለም። ያደረግሃቸው አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ፥ አቤቱ፥ በፊትህም ይሰግዳሉ፥ ስምህንም ያከብራሉ፤ አቤቱ፥ ድንቅ የምታደርግ አንተ ታላቅ ነህና፥ አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና።* (መዝ. 86፡8-10)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ዘማሪው የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ መሆኑን የሚያሳዩት የትኞቹ ቃላት ናቸው?

   አቤቱ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፥ እንደ ሥራህም ያለ የለም። ያደረግሃቸው አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ፥ አቤቱ፥ በፊትህም ይሰግዳሉ፥ ስምህንም ያከብራሉ፤ አቤቱ፥ ድንቅ የምታደርግ አንተ ታላቅ ነህና፥ አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና። (መዝ. 86፡8-10)።

7. የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር አምጡ፥ ክብርንና ኃይልን ለእግዚአብሔር አምጡ። ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ፤ ቍርባንን ይዛችሁ በፊቱ ግቡ፤ በቅድስናው ስፍራ

ለእግዚአብሔር ስገዱ። (1ኛ ዜና 16፡28-29)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ዘማሪው የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ መሆኑን የሚያሳዩት የትኞቹ ቃላት ናቸው?

> *"የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር አምጡ፥ ክብርንና ኃይልን ለእግዚአብሔር አምጡ። ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ፤ ቍርባንን ይዛችሁ በፊቱ ግቡ፤ በቅድስናው ሰፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ።" (1ኛ ዜና 16፡28-29)።*

8. ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ። (ራዕይ 15፡4)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ዘማሪው የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ መሆኑን የሚያሳዩት የትኞቹ ቃላት ናቸው?

> *"ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።" (ራዕይ 15፡4)።*

ለማጠቃለል ከእነዚህ መዝሙሮች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ዘምሩ። በአማራጭ፣ እንደ የመደምደሚያ ጸሎት ለማንበብ አንድ መዝሙር ይምረጡ።

1. "የጸጋውን ዙፋን እዩ!"
2. "ነፍሴ ነይ ልብስሽን አዘጋጅ"
3. "ክብር ለአብ ይሁን"
4. "ሰማያት ክብርህን ይናገራሉ"
5. "የጌታ ጸሎት"
6. "ጣፋጭ የጸሎት ሰዓት"

ክፈል IX
የጌታ ጸሎት

ምዕራፍ 2
የእግዚአብሄር መንግስትና ፈቃድ

አላማ የእግዚአብሔርን መንግስት ድል ለመለማና ለፈቃዱ ለመገዛት

ካቴኪዝም* ጥ. በሁለተኛው ልመና የምንጸልየው ስለ ምንድነው?

መ. በሁለተኛው ልመና፣ ማለትም፣ "መንግሥትህ ትምጣ"፣ ስንል የጸጋው መንግሥት ወደፊት እንዲራመድና፣ የሰይጣን መንግሥት እንዲፈርስ እንጸልያለን። እኛና ሌሎች ወደ እርስዋ በመምጣት በውስጧ እንድንቆይ፣ የክብር መንግሥትም ትፈጥን ዘንድ ነው።

ጥ. በሶስተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?

ሀ. በሦስተኛው ልመና፣ ማለትም "ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች በምድርም ትሁን" ስንል መላእክት በሰማይ እንደሚያደርጉት ሁሉ በእግዚአብሔር

ጸጋ ፈቃዱን እንድናውቅ፣ እንድንታዘዝና በሁሉም ነገር ለመገዛት ፈቃደኞች እንድንሆን እንጸልያለን።

የቃል ጥቅስ የሐዋርያት ሥራ 26፡18 “የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።”

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ</u>

ዓላማ

የእግዚአብሔርን መንግሥት ድል ለመፈለግና ለፈቃዱ ለመገዛት።

ካቴኪዝም

ጥ. በሁለተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. በሁለተኛው ልመና፣ ማለትም፣ *መንግሥትህ ትምጣ፣* በሚለው የሰይጣን መንግሥት እንድትፈርስ እንጸልያለን። እና የጸጋው መንግሥት ወደፊት እንዲራመድ፣ እኛና ሌሎች ወደ እርስዋ በመምጣት በውስጧ እንድንቆይ፣ የክብር መንግሥትም ትፈጥን ዘንድ እንጸልያለን።

ጥ. በሶስተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. በሦስተኛው ልመና፣ ማለትም “ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች በምድርም ትሁን” ስንል መላእክት በሰማይ እንደሚያደርጉት ሁሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ፈቃዱን እንድናውቅ፣ እንድንታዘዝና በሁሉም ነገር ለመገዛት ፈቃደኞች እንድንሆን እንጸልያለን።

መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ታዳጊዎች እነዚህን ቃላት እንዲፈልጉ ጠይቃቸው፡ መንግሥት፣ ጸጋ፣ የላቀ፣ ክብር እና ፈቃድ። የእያንዳንዱን ፍች እንዲያነቡ እና ከዚያም የተጻፈውን ፍቺ ሳያዩ ቃሉን በራሳቸው አባባል ለመተርጎም ይሞክሩ። እያንዳንዱን ቃል በደንብ እስኪረዱት ድረስ ትርጉሙን በማንበብ እና በራሳቸው አባባል በየተራ እንዲገልጹ ንገራቸው። የተጻፈውን ፍች በእያንዳንዱ ጊዜ በቀላሉ የሚደጋግሙ ከሆነ በመጀመሪያ የሁሉንም ቃላት ፍችዎች እንዲያነቡ ምራቸው፤ ከዚያም ሳያዩ የሁሉንም ቃላት ፍች በራሳቸው አባባል ይግለጹ። በመቀጠል፣ የካቴኪዝም ጥያቄዎችን እና መልሶችን እንደገና ካነበቡ በኋላ፣ ስለ መቅድም እና የመጀመሪያ ልመና የቻሉትን ያህል በራሳቸው አባባል እንዲያብራሩ ጠይቃቸው።

ከዚያም ታዳጊዎች የቃላቶቹን በተሻለ ሁኔታ በመረዳት በማብራራት ከላይ ያሉትን ሁለቱን የካቴኪዝም ጥያቄዎች እና መልሶች በራሳቸው አባባል እንዲጽፉ አስተምቸው። ከዚህ በታች እንደገና ለመፃፍ የተሞከረው ምሳሌ ነገሩ ምን ሊመስል እንደሚችል ያሳያል።

ጥ፦ "መንግሥትህ ትምጣ" በሚለው በሁለተኛው ልመና ውስጥ ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. የሰይጣንን መንግስት በምድር ላይ እንዲያፈርስ፣ የተመረጡትን በማደስ እና በመጠበቅ የእግዚአብሔር መንግስት በምድር ላይ ወደፊት እንዲራመድና ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ምርጦቹን ወደ ዘላለማዊ መንግስቱ ለማፍለስ ያለውን ጊዜ እንዲያሳጥር ትለምናላችሁ።

ጥ፦ "ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" በሚለው ሦስተኛው ልመና ስለምን እንጸልያለን?

መ. የሰማይ መላእክት እንደሚያደርጉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ፀጋ እንድናውቅ፣ እንድትታዘዝና ለፈቃዱ እንድትገዛ እንድትፈቅድ እንጸልያለን።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ</u>

ታዳጊዎች እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚደግፈውን የካቴኪዝም ሐረግ(ዎች) እንዲለዩ ጠይቃቸው።

መዝሙረ ዳዊት 67:1-2 እግዚአብሔር ይማረን ይባርከንም፥ ፊቱንም በላያችን ያብራ፤በአሕዛብ ሁሉ መካከል ማዳንህን፥ መንገድህንም በምድር እናውቅ ዘንድ።

የጸጋው መንግሥት ወደፊት እንዲራመድ፣ እኛና ሌሎች ወደ እርሷ እንድንገባ መጸለይ...

መዝሙረ ዳዊት 68፡1 "እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ ጠላቶቹ ከፊቱ ይሸሹ።"

የሰይጣን መንግሥት እንዲፈርስ መጸለይ

መዝሙረ ዳዊት 103:20 ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።

መላእክት በሰማይ እንደሚያደርጉት ለማወቅ፣ ለመታዘዝ እና በሁሉም ነገር ለፈቃዱ ለመገዛት መጸለይ ...

መዝሙረ ዳዊት 119:33-36 አቤቱ፥ የሥርዓትህን መንገድ አስተምረኝ፥ ሁልጊዜም እፈልገዋለሁ።እንዳስተውል አድርገኝ፥ ሕግህንም እፈልጋለሁ፤ በፍጹም ልቤም

እጠብቀዋለሁ። እርስዋን ወድጃለሁና የትእዛዝህን መንገድ ምራኝ። ልቤን ወደ ምስክርህ አዘንብል፥ ወደ ስስትም አይሁን።

ለማወቅ፣ ለመታዘዝ፣ እና በሁሉም ነገር ለፈቃዱ ለመገዛት መጸለይ...

ሮሜ 10፡1 ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው።

የጸጋው መንግሥት ወደፊት እንዲራመድ፣ እኛና ሌሎች ወደ እርሷ እንድንገባ መጸለይ...

ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 2፡13 ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።

እግዚአብሔርን እንድናውቅ፣ እንድንታዘዝ እና ለፈቃዱ እንድንገዛ ፈቃደኞች እንድንሆን እንዲረዳን መጸለይ

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡1 ቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፥ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ።

የጸጋው መንግሥት ወደፊት እንዲራመድ፣ እኛና ሌሎች ወደ እርሷ እንድንገባ መጸለይ...

የዮሐንስ ራእይ 22፡20 ይህን የሚመሰክር። አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና። የክብር መንግሥት እንዲፋጠን መጸለይ።

<u>የካቴኪዝም ጥያቄዎች</u>

1. ሁለተኛው ልመና የሚያመለክተው ስለ የትኞቹ ሦስት መንግሥታት ነው?

የሰይጣን መንግሥት፣ የጸጋ መንግሥት፣ እና የክብር መንግሥት

2. ስለ እያንዳንዱ መንግሥት ምን መጸለይ አለብን?

የሰይጣን መንግሥት እንዲፈር እንጸልያለን።

የጸጋው መንግሥት እንዲያድግ እንጸልያለን።

የክብር መንግሥት በቅርቡ እንድትመጣ እንጸልያለን።።።

3. በህይወታችሁ ውስጥ ሁነቶችን እና ውሳኔዎችን እንዲቆጣጠር የምትጸዩት ወደ ማን ነው?

በሁሉም የሕይወትህ ዘርፍ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ጸልይ። ምናልባት የራስህን ፈቃድ እንድታደርግ እግዚአብሔር እንዳይፈቅድልህ ጸልይ።

4. የራሳችሁን ፈቃድ እንድትተዉ እና በምትኩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ እንድትመኙ የሚያደርጋችሁ ምንድን ነው?

ሰሮጌው ኃጢአትህ ተፈጥሮ የራሱን ፈቃድ ይፈልጋል (ክፍል III፣ ምዕራፍ 2)። የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው "በሁሉም ነገር ለማወቅ፣ ለመታዘዝ እና ለፈቃዱ ለመገዛት እንድንችል ፈቃደኛ የሚያደርገን።" (ሰጮር ካቴኪዝም #103)

5. ለሚከተሉት ችሎታዎች እና ፈቃደኝነት መጸለይ አለባችሁ እንዴት ነው?

ሀ. በሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አለብን!

የተገለጠውን ፈቃዱን የያዘውን ቃሉን የምታጠኑበትን ጊዜ፣ ሃብቶች እና ፍላጎት እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ለምኑት። እንዲሁም፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ማለት እንደሆኑና በህይወታችሁ እንዴት እንደምትተገብሯቸው እንዲያስተምራችሁ መንፈስ ቅዱስን ጠይቁት።

ለ. በሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ መታዘዝ አለብን!

በየቀኑ የእርሱን ፈቃድ ለመከተል ድፍረትን፣ ጥንካሬን እና ቁርጠኝነትን እንዲሰጥህ ጸልይ።

ሐ. በሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት አለብን!

የተገለጠውን ፈቃድ በደስታ መንፈስ እንድትፈጽምና በትክክለኛው አመለካከት ልብህን እንዲያለሰልስ ለምነው። እንዲሁም ስውር ፈቃዱ ባልተገለጸልህ ጊዜ በትዕግስት እንድትቀበል እግዚአብሄር እንዲረዳህ ለምነው።

6. በመዝሙር 103:20 መሠረት የእግዚአብሄርን ፈቃድ በሰማይ የሚታዘዙ እነማን ናቸው?

"እግዚአብሔርን አመስግኑት መላእክቱ ትእዛዙንም የምታደርጉ ቃሉንም የምትጠብቁ ኃያላን" (መዝ.103:20)። ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሰማይ ይታዘዛሉ።

የቃል ጥቅስ

የሐዋርያት ሥራ 26፡18 "የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።"

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሦስት መንግሥታት ይናገራል፡-

ሀ. ያልዳኑትን የሰው ልጆች ምድር እና ልብ የሚገዛው የሰይጣን መንግሥት፣

ለ. በምድራዊ ቅዱሳን ነፍሳት ውስጥ የሚገዛው የእግዚአብሔር የጸጋ መንግሥት፣ እና

ሐ. የእግዚአብሔር የወደፊት ፍጹም የክብር መንግሥት፣ የተመረጡት ዘላለማዊ መኖሪያ መንግሥተ ሰማያት በመባል ይታወቃል።

ሁለተኛው ልመና፣ "መንግሥትህ ትምጣ"፣ እግዚአብሔር የሰይጣንን አገዛዝ እንዲያጠፋ፣ የጸጋውን መንግሥት ወደፊት እንዲያራምድ፣ እና የእግዚአብሔርን የከበረ መንግስት እንዲያፋጥን ይጠይቃል። የቃል ጥቅስ የሰይጣንን መንግሥት ከጸጋው መንግሥት ጋር በማነፃፀር የክብር መንግሥት የክርስቲያን የመጨረሻ ርስት አድርጎ ይጠቁማል።

<u>የሰይጣን መንግሥት</u>

ሰይጣን አዳምና ሔዋንን በማታለል ከታመነው እና ታማኝ ከሆነው ፈጣሪያቸው ለይቶ ወደ ጨለማ መንግሥት አሳታቸው። (ክፍል ፫፣ ምዕራፍ 1)። ከዚያ አስከፊ ቀን ጀምሮ "የውሸት አባት" (ዮሐንስ 8: 44) በምድር ላይ በሚኖሩት ሰዎች መካከል መንፈሳዊ እንዲታወሩና፣ በሚያጠፋ ኃጢአትና በአስከፊ መከራ ውስጥ በየቀኑ እንዲዳክሩ ያደረጋቸው ክፉ ጨካኝ አገዛዝ ነው። (ክፍል 3፣ ምዕራፍ 2) . ብዙውን ጊዜ "የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል" (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡14) ይህ ርኩስ መንፈስ ምድራዊ ደስታን፣ ዝናን፣ ተጽዕኖን፣ ክብርን እና ሀብትን ይሰጣል። ነገር ግን ይህ ሁሉ ከፍተኛ ኃይሉን እና ተጽእኖውን ለማቆየት የተነደፈ የውሸቶች ዘዴ ነው። ዘመኖቹ የተቆጠሩ ናቸው። እንዲሁም ሁሉም ተገዢዎቹ የዘላለም ፍርድ ይጠብቃቸዋል። (ማቴዎስ 25፡41)። ባጭሩ፣ ክፉው መንግሥቱ ያከትማል፣ ቅዱሳን ደግሞ ስለጥፋቱ በትክክል ይጸልያሉ።

የሰይጣን ተገዢዎች የመዳንን ብርሃን ባለማወቃቸው በመንፈሳዊ ድንዛዜ ውስጥ ሆነው ይንከራተታሉ። በጣዖት አምልኮ ውስጥ የተዘፈቁ፣ የሰውን ምክንያታዊነት፣ ሳይንሳዊ ኢምፔሪቲዝምን፣ የህብረተሰቡን ወግና ሰፊውን ባህላዊ ጉዳዮችን በጭፍን ያከብራሉ። እንደነዚህ ያሉት የሐሰት አማልክት ተስፋ ከማድረግ በተጨማሪ ነፍሳትን ያታልላሉ እንዲሁም ያስራሉ። ምእመናኖቻቸው በሲኦል የአበባ ማር ላይ በመንፈስ ሰክረው የራሳቸውን ባርነት፣ የሰይጣንን ገዢነት እና የመጨረሻውን ጥፋት ማወቅ አልቻሉም።

ያልተለወጡ ነፍሳት ጨረቃ በሌለበት ሌሊት ካለ ጥልቅ ዋሻ ይልቅ በጨለማ ውስጥ ናቸው። ምንም አይነት የተስፋ የሚሰጥ የብርሀን ብልጭታ በድቅድቅ እና ጥቁር ዋሻዎች ውስጥ አያበራም። የተረገሙና የተበላሹ መናፍስት ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ክፉ ድርጊቶች፣ አስተሳሰቦችን እና አመለካከቶችን ያፈሳሉ። በፈቃዳቸው በሰይጣን ሞግዚትነት እና ስልጣን ስር ሆነው በጨለማው መንግስት ውስጥ ያገለግላሉ። በእርግጥም፣ “ሰዎች ሥራቸው ክፉ ስለ ሆነ በብርሃን ፈንታ ጨለማን ይወዳሉ” (ዮሐንስ 3፡19)። ከክርስቶስ የመቤገርት ጸጋ ተለይተው ለዘላለም ጠፍተዋል።

<u>የጸጋው መንግሥት</u>

የአዳም ውድቀት የሰው ልጆችን ሁሉ ወደ ሰይጣን ግዛት ውስጥ አስገባው (ክፍል III፣ ምዕራፍ 2)። ነገር ግን “በትክክለኛው ጊዜ [በታሪክ]፣ … ክርስቶስ ለኃጢአተኞች ሞተ” (ሮሜ 5፡6)። ኢየሱስ ነፍሱን እንደ “የእግዚአብሔር በግ” በፈቃዱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ የኃጢአትን አስከፊ ዋጋ ከፍሏል። ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መስዋዕትነት መቤገርት አስችሎታል። (ክፍል IV፣ ምዕራፍ 1)። በእርሱ የተመረጡት ከሰይጣን የተስፋ መቁረጥ መንግሥት አምልጠው ወደ እግዚአብሔር የጸጋ መንግሥት ጽድቅ ገቡ።

ይህ ሥር ነቀል የታማኝነት ለውጥ ከምን ጋር ሊወዳደር ይችላል? ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላ መንግሥት የተደረገውን አስደናቂ ሽግግር በምክንያታዊነት የሚገልጸው የትኛው ምድራዊ ሁኔታና ለውጥ ነው? የቃል ጥቅሱ የሚያመለክተው ቀደም ሲል የተዘጉ ዓይኖችን ሁኔታ ነው ይህም መንፈሳዊ እውርነትን እና ብርቱ ጨለማን ያመለክታል። “እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስ አፍስሶባችኋል ዓይኖቻችሁን ነቢያትንም ጨፍኖባችኋል ራሶቻችሁን ባለ ራእዮችን ሸፍኖባችኋል።” (ኢሳ 29፡10)። "ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ!" (ማቴዎስ 6:23) “ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ጆሮቻቸውም እንዳይሰሙ እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው ተብሎ ተጽፎአል” (ሮሜ 11፡8)። በአንጻሩ መንፈስ ቅዱስ ዓይኖችን ይከፍታል፣ መንፈሳዊ ራዕይን ይሰጣል እናም ነፍስን ያበራል። “ዕውሮችንም በማያውቁት መንገድ አመጣቸዋለሁ፥ በማያውቁትም ጎዳና እመራቸዋለሁ፤ በፊታቸውም ጨለማውን ብርሃን አደርጋለሁ፥ ጠማማውንም አቀናለሁ። ይህን አደርግላቸዋለሁ፥ አልተዋቸውምምና።” (ኢሳ 42፡16)። "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።” (1ኛ ጴጥሮስ 2፡9-10)። በእግዚአብሔር ከተማ እና በክርስቲያናዊ አስተምህሮ (1887) ቅዱስ አውግስጢኖስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- “ሰዎች በክርስቶስ ስም ከእነዚህ ርኩሳን መናፍስት የገሃነም ጭቆናና በቅጣታቸው ተካፋይ ከመሆን በክርስቶስ ስም ይድናሉ፤ እናም እግዚአብሔርን ካለመፍራት ጨለማ ከፍ ወዳለ ጤናማው የአምልኮ ብርሀን ይወጣሉ።”

ሰዎችን ወደ ጸጋው መንግሥት እንዲጠራ መንፈስ ቅዱስን ለምኑት። መንፈሳዊ ጨለማን ወደ ሰማያዊ ብሩህነት በመቀየር ዓይነ ስውርነታቸውን እንዲከፍት እግዚአብሔርን ለምኑት። “እግዚአብሔር [የሰይጣን ተገዢዎችን] እውነትን ወደ ማወቅ እንዲመራቸው ንስሐ እንዲሰጣቸው፣ ወደ አእምሮአቸውም ተመልሰው ፈቃዱን እንዲያደርጉ ከማረካቸው ከዲያብሎስ ወጥመድ እንዲያመልጡ ለምኑ። 2፡26)። “መንግሥትህ ትምጣ” ብላችሁ ጸልዩ።

<u>የክብር መንግሥት</u>

ማንም እንዳይጠፋ ጌታ በጸጋው መንግሥት ያሉትን ሁሉ ይጠብቃል። ቅዱሳን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የክብር መንግሥት ይገባሉ። (ክፍል 5፣ ምዕራፍ 6)። “ያጸደቃቸውን ደግሞ አከበራቸው” (ሮሜ 8፡30) በእርግጥም የክብር መንግሥት በጸጋ መንግሥት ውስጥ ላሉት የመጨረሻው ርስት እና ሽልማት ነው። “ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።” (ሮሜ 8:17) የቃል ጥቅሱ “የኃጢአትን ስርየት የሚቀበሉ”፣ ወደ የጸጋው መንግሥት ኣንደሚገቡ፣ እንዲሁም “በእምነት ከተቀደሱት መካከል [“ርስትን” ይቀበላሉ፣ ይህም የክብርን መንግሥት ያካትታል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ እግዚአብሔር የክብር መንግሥት ለመግባት ጓጉቷል። “[ከዚህ ሕይወት] ልሄድ ከክርስቶስም ጋር [በገነት] ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና” (ፊልጵስዩስ 1፡23)። ሰማይ ለእግዚአብሄ ሕዝቦች ያቀረበውን አስደናቂ ነገር ለማድነቅ አሁን ከምትኖርበት የሰይጣን ግዛት ጋር አወዳድር። ምድራዊ ሕይወት በብዙ መንገዶች ውብ ቢሆንም በክርክር፣ በሙስና፣ በጭቆና፣ በግፍ አገዛዝ፣ በተስፋ መቁረጥ፣ በጸጸት፣ በልብ ሕመም፣ በበሽታ፣ በሥቃይ፣ በፍርሃትና በሞት የተሞሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ከባድ ፈተናዎችን ያካትታል። በአሮጌው የኃጢያአታዊ ተፈጥሮህ እና በሰይጣን ረቂቅ ማታለያዎች ምክንያት፣ እንዲሁም ያለማቋረጥ ከኃጢአተኛ ፈተናዎች ጋር ትታገላለህ እናም እሺ ስትል የኃጢአትን ጨካኝ ውጤቶች ትሸከማለህ። ባጭሩ፣ የሰይጣን መንግሥት በጸጋው መንግሥት ውስጥ ለተቤጁ ቅዱሳን እንኳን ብዙ ደስ የማይል ነገርን ይፈጥራል።

ክርስቶስ ግን ህዝቡን ወደ ክብር መንግስት ሲያመጣ ሰይጣንን ሙሉ በሙሉ ይገለብጠዋል። አንዴ ቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ከገቡ፣ ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር ቅዱስ ህልውና ይኖራሉ እናም ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይገናኛሉ። ዳግመኛ አይጨነቁም፣ አይፈሩም፣ አይጎዱም፣ አያለቅሱም፣ ኃጢአተኛም አይሆኑም። “የእግዚአብሔር ማደሪያ በሰዎች መካከል ይሆናል፥ ከእነርሱም ጋር ይኖራል። እነሱ የእርሱ ሕዝብ ይሆናሉ፣ እና እግዚአብሔር ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል። እንባን ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል። ሞት ወይም ኀዘን ወይም ልቅሶ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና” (ራዕይ 21፡3-4)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚያገኙት መልካምነት፣ ጽድቅ፣ ንጽሕና፣ ደስታ፣ ደህንነት እና ሰላም ብቻ ነው።

ኢየሱስም፣ “እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ!” አለ። (የዮሐንስ ራእይ 22:7) ዳግም ምጽዐቱ የተመረጡትን ወደ ዘላለማዊ ክብር ያስገባቸዋል። ቅዱሳን ይህንን መንግሥት የሚያፋጥን ማንኛውንም ነገር በጣም ሊመኙት ይገባል። ስለዚህ፣ “መንግሥትህ ትምጣ” የሚለውን ሁለተኛውን ልመና በታማኝነት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አቅርቡ።

<u>የቃል ጥቅስ ጥያቄዎች</u>

1. የሰይጣንን መንግሥት ተመልከት።

ሀ. “ዓለም ሁሉ በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን” (ሀዮሐንስ 5:19) የሰይጣን መንግሥት የት ነው ያለው?

የሰይጣን መንግሥት ምድራዊ ነው; ባልዳነው የሰው ልጆች ልብ ውስጥ ነግሷል። እነዚህን ጥቅሶች ደግሞ ተመልከት፡- “የዚህ ዓለም ገዥ [ሰይጣን] ይመጣል” (ዮሐንስ 14፡30)። “ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ” (ራዕይ 12፡9)።

ለ. “ኃጢአት በአንድ ሰው [በአዳም] ወደ ዓለም ገባ፣ በኃጢአትም ሞት፣ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።” (ሮሜ 5:12) አንድ ሰው ወደ ሰይጣን መንግሥት የሚገባው እንዴት ነው?

አዳም የሰው ልጅ ወካይ ራስ እንደመሆኑ መጠን የመጀመሪያውን ኃጢአት ሠርቷል፤ ይህም አሁን ሁሉንም ሰው አበላሽቷል። በተጨማሪም እያንዳንዱ ሰው ከአዳም በወረሰው ብልሹ ተፈጥሮ የተነሳ ኃጢአትን ይሠራል። ስለዚህ የሰው ልጅ ወደ ሰይጣን መንግሥት የሚገባው በቀዳሚው (original sin) ኃጢአት እና በሰራው እውነተኛ ኃጢአት ነው። (ክፍል III)

ሐ. “በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።” (ኤፌሶን 2፡2)። የሰይጣንን መንግሥት የሚያገለግለው ማን ነው?

የእግዚአብሔርን ነፃ የመዳን ስጦታ የማይቀበሉ የሰይጣን መንግሥት አገልጋዮች ናቸው፣ የሞራል ህግን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አምነው ንስሃ እንዲገቡ ይጥራሉ።

መ. "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን።" (ሮሜ 5፡1-2)። የሰይጣን መንግሥት አባል የሆኑ ሰዎች ፈጽሞ ሊተዉት ይችላሉ?

አዎን፣ መንፈስ ቅዱስ በእምነት እና በንስሃ፣ እና በጸጋው መንግስት የተመረጡትን ከሰይጣን መንግስት ይጠራቸዋል።

ሠ. "ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።" (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4)። ለምን ሁሉም ሰው ከሰይጣን መንግሥት አያመልጥም?

ያልተዋጁት በፍፁም መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው ተሸፍኖ በጨለማ ውስጥ ይኖራሉ። እግዚአብሔር ካላበራላቸው ወደ ጸጋው መንግሥት ማምለጥ አይችሉም።

ረ. "*ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።*" (ራዕይ 20፡10)። የሰይጣን መንግሥት የሚጠፋው መቼ ነው?

እግዚአብሔር ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሰይጣንንና መንግስቱን ያጠፋቸዋል።

2. የእግዚአብሔርን የጸጋ መንግሥት አስቡ፡-

ሀ. "*የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም*" (ሮሜ 14፡17)። "የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤ደግሞም። እንኂት በዚህ ወይም። እንኂት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና" (ሉቃስ 17፡ 20-21)። የጸጋው መንግሥት ወዴት ነው?

የጸጋው መንግሥት ዳግመኛ የተወለዱትን ማለትም የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያንን ያቅፋል። (ክፍል V፣ ምዕራፍ 2)። ውጫዊ፣ የሚታይ መንግሥት ሳይሆን በእግዚአብሔር በተዋጁ ቅዱሳን ነፍሳት ውስጥ ያለ ነው።

ለ. "[አብ] ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ [ክርስቶስ] ሊነግሥ ይገባዋልና" (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡25)። "[ኢየሱስ] በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት። የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው።" (ራዕይ 19፡16) የጸጋውን መንግሥት የሚገዛው ማን ነው?

ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋው መንግሥት ላይ ነግሷል። (ክፍል 4፣ ምዕራፍ 4)።

ሐ. “[አብ] እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።” (ቆላስይስ 1፡13)። አንድ ሰው ከገዥዎቹ አንዱ ሆኖ ወደ ጸጋው መንግሥት እንዴት ይገባል?

መንፈስ ቅዱስ በእምነት፣ በንስሃ ወደ ጸጋ መንግስት የተመረጡትን ከሰይጣን መንግስት ይጠራል። አንድ ሰው ከጨለማ ወደ ብርሃን ሲመጣ፣ አጭር ካቴኪዝም #102 ለውጡን የጸጋውን መንግሥት ማራመድ እንደሆነ ይገልፃል። ይህን ክፍል ደግሞ ተመልከት፡- “እኔ [ኢየሱስ] ግን በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።ኃይለኛ ሰው ጋሻና ጦር ይዞ የራሱን ግቢ ቢጠብቅ፥ ያለው ገንዘቡ በሰላም ይሆናል፤ከእርሱ ይልቅ የሚበረታ መጥቶ ሲያሸንፈው ግን፥ ታምኖበት የነበረውን ጋሻና ጦር ይወስድበታል ምርኮውንም ያካፍላል” (ሉቃስ 11፡20-22)።

መ. “ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው።” (ዮሐንስ 6፡39)። “ያመንሁትን አውቃለሁ፤ የሰጠሁትንም አደራ በዚያ ቀን ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቻለሁ” (2ጢሞ. 1፡12)። ወደ ጸጋው መንግሥት የሚገቡት ወደ ሰይጣን መንግሥት ሊመለሱ ይችላሉ?

አይ! እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል፣ በምድራዊ ሕይወታቸው ሁሉ እንዲጸኑ ያደርጋቸዋል። (ክፍል V፣ ምዕራፍ 6)።

3. የእግዚአብሔርን የወደፊት የክብር መንግሥት አስብ፡-

ሀ. “ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።” (2ኛ ጴጥሮስ 3፡13)። የክብር መንግሥት ምንድን ነው?

የክብር መንግሥት የተዋጁት ለዘላለም የሚኖሩበትን የክርስቶስን ፍጹም መንግሥት ያመለክታል። ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን መንግሥት መንግስተ ሰማይ፣ ገነት፣ ክብር እና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ብለው ይጠሩታል።

ለ. “ያጸደቃቸውን ደግሞ አከበራቸው” (ሮሜ 8፡30) አንድ ሰው እንዴት ወደ ክብር መንግሥት ይገባል?

ማንም አስቀድሞ በጽድቅ ወደ ጸጋው መንግሥት ካልገባ ወደ ክብር መንግሥት ሊገባ አይችልም። (ክፍል V፣ ምዕራፍ 3)። የጸጋው መንግስት አባል የሆኑት ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ እና ስጋቸውን በመጨረሻው ቀን ሲያስነሳ ወደ ክብር መንግስት ይገባሉ።

ሐ. “ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም” (ኢሳይያስ 9፡7) “እርሱ [ኢየሱስ] እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።” (ሉቃስ 1፡32-33) የክብር መንግሥት እስከ መቼ ነው የሚቆየው?

የክብር መንግሥት ለዘላለም ይኖራል።

4. ባጭሩ ካቴኪዝም እንደተብራራው፣ ጆምስ ፊሸር የጸጋ እና የክብር መንግስትን እንደ ሁለት የአንድ መንግስት ግዛቶች አድርጎ ይመለከታቸዋል፡ “ፀጋ የክብር መጀመሪያ ነው፣ ክብር ደግሞ የፀጋ ማጠናቀቂያ ነው። ይህ የሱ አባባል ምን ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

አንድ ሰው በክርስቶስ በማመን እና በእውነተኛ ንስሃ ወደ ጸጋው መንግስት ሲገባ፣ አዲሱ ህይወቱ ስለወደፊቱ የክብር መንግስት ፍንጭ ይሰጠዋል። ወደ ክብር መንግሥት እስኪገቡ ድረስ በምድራዊ ሕይወታቸው ሁሉ ጸጋ በነፍሳቸው ውስጥ ይሠራል። ስለዚህም ዘላለማዊ ክብር የእግዚአብሔር ጸጋ የመጨረሻ ውጤት ነው።

5. የሚከተሉት ምንባቦች በዋነኝነት የሚያመለክቱት የትኞቹን መንግሥታት ነው?

ሀ. “ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ያን ጊዜ እናንተ ደግሞ እርሱ ጋር በክብር ይገለጣሉ” (ቆላስይስ 3፡4)

የክብር መንግሥት

ለ. "እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት። ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።” (1ዮሐ. 1፡5-7)።

የጸጋው መንግሥት

ሐ. “ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ

ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ" (1ዮሐ. 2፡15-17)።

የሰይጣን መንግሥት

መ. "ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል። ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፥ ፀሐይም ትኵሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም፤ በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል" (ራዕይ 7፡15-17)።

የክብር መንግሥት

ሠ. "ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ" (ራዕይ 22፡5)።

የክብር መንግሥት

ረ. "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና" (ራዕይ 22፡20)

የክብር መንግሥት

6. "ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ" (ሐዋ. 26፡18)። በሐዋርያት ሥራ 9 ላይ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ እይታን የተቀበሉ እነማን ናቸው?

ሳኦል ይባል የነበረው ሐዋያው ጳውሎስ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "ፈቃድህ ይሁን" ብለው እንዲጸልዩ አስተምሯቸዋል። ከእነዚያ ደቀ መዛሙርት አንዱ የሆነው ሐዋርያው ዮሐንስ በኋላ ቅዱሳን እግዚአብሔርን "እንደ ፈቃዱ" እንዲለምኑ መክሯቸዋል። (1ዮሐ. 5፡14)። እነዚህ ክፍሎች ሦስት ጥያቄዎችን ያስከትላሉ፡- (ሀ) "የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው?" (ለ) "የእግዚአብሔር ፈቃድ

በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ምን ይመስላል?" እና (ሐ) "ለእግዚአብሔር ፈቃድ የምትጸልየው እንዴት ነው?"

<u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት</u>

ጌታ እንድታደርጉ የሚፈልገውን ለማወቅ እና በፈቃደኝነት መንፈስ ለማድረግ እንድትችሉ ብዙ ደስታን፣ ሰላምን፣ ዋስትናን፣ እርካታን፣ ጥንካሬን እና የዓላማ ስሜትን ይሰጣል። ሆኖም አንዳንድ ክርስቲያኖች በዋነኛነት ወሳኝ በሆኑ ውሳኔዎች፣ አጠቃላይ መመሪያዎች፣ ሃይማኖታዊ ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች ወይም የግል ስሜቶች ላይ በማተኮር እግዚአብሄር ለሕይወታቸው ያለውን ልዩ ፈቃድ ለማወቅ ይታገላሉ። ሌሎች ደግሞ ዘላለማዊ እቅዱ ጋር እንዴት እንደሚስማሙ፣ ምን ውሳኔዎች እንደሚያደርጉ እና እግዚአብሔር ሊሳካ የሚፈልጋቸውን ትልልቅ ነገሮች ሊያስቡ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ እነዚህ ሰዎች የጌታን ፈቃድ ሊፈልጉ የሚችሉባቸው ጥቂት ወሳኝ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-

ሀ. " እኔ በንግድ ትምህርት ቤት፣ በአካስተኛ ክርስቲያን ኮሌጅ፣ ወይስ

በዋናው የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ትምህቴን ልከታተል?"

ለ. "መንፈሳዊ ስጦታዎቼን እንዴት መጠቀም አለብኝ?"

ሐ. "ወደ መጋቢነት፣ ወደ ህግ ወደ ውትድርና ልግባ?"

መ. "ማንን ላግባ?"

ሠ. "ከኔ የተወለደ ልጅ ይኑረኝ፣ ከሌላ ወስጀ ላሳድግ ወይስ ያለ ልጅ ልኑር?"

ረ. "ልጆቼን ወደ ግል ትምህርት ቤት ወይስ ወደ የህዝብ ትምህርት ቤት መላክ አለብኝ?"

ሰ. "በሳን ፍራንሲስኮ፣ በናሽቪል፣ በቶሌዶ ወይስ በካራቺ ልኑር?"

ሸ. "የሰንበት ትምህርት ቤት በማስተማር፣ ከስደተኞች ጋር በመሥራት፣ ዲያቆን ሆኜ በማገልገል፣ ወይስ በአጭር ጊዜ ተልእኮዎች ልሳተፍ?

ቀ. "መቼ ጡረታ መውጣት አለብኝ እና ከወጣሁ በኋላስ ምን ማድረግ አለብኝ?"

ለእነዚህና መሰል ጥያቄዎች ክርስቲያኖች መለኮታዊ ምክር መጠየቃቸው የተገባ ነው። ቢሆንም፣ አንዳንድ አማኞች፣ በጊዜ ሂደት፣ አሁንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳመለጣቸው ይሰማቸዋል። በጸሎት ቢፈልጉትም፣ በአእምሯቸው ግን ያመለጣቸው ይመስላል። እንዲያውም በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ምርጡን በማያዳግም ሁኔታ እንዳመለጣቸው ሊያስቡ ይችላሉ፣

በዚህም ተስፋ ቆርጠዋል እና እነሱ እርካታ የላቸውም። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከትላልቅ ጉዳዮች፣ ውሳኔዎች እና መመሪያዎች ጋር ብቻ የተያያዘ ነው የሚለውን አመለካከት ጨምሮ የተሳሳቱ ስሜቶችና አስተሳሰቦችና የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ የኋለኛው እሳቤ ግራ የሚያጋባ እና ለእግዚአብሔር ተጨማሪ ነገሮችን ያላደረጉትን፣ እንደሌሎች የህዝብ እውቅና ያላገኙትን፣ ወይም የሰማይ መለኮታዊ በረከት ያልቀመሱትን ሊያናጋ ይችላል።

እነዚህ ተስፋ የቆረጡ ቅዱሳን ሁሉን ቻይ በሆነው በተሰወረው ፈቃድ እና በተገለጠው ፈቃድ መካከል በመለየት ከመጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ፈቃድ" ምን ማለት እንደሆነ መማር አለባቸው። "ምስጢሩ [ስውርነቱ] ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እንከተል ዘንድ ለእኛና ለልጆቻችን ለዘላለም ነው" (ዘዳ 29፡29)።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች አስቀድሞ የማይገልጠው ድብቅ ፈቃድ አለው። "ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቅ የለም" (1ኛ ቆሮንቶስ 2፡11)። እግዚአብሔር ፍጥረትን በሚመራበት ጊዜ፣ በተለይም ለተመረጡት በፍቅር ሲሰጥ ለማድረግ የወሰናቸው ምስጢራዊ ወይም የማይታወቁ ነገሮችን ሁሉ ያካትታል። "ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ" (ኢሳ 46፡10)። እርሱ "እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ" (ኤፌሶን 1፡11)። የእግዚአብሔር ስውር ፈቃድ በመጨረሻ ለክርስቲያኖች ጥቅም ይገለጣል፤ እግዚአብሔር ለነሱ ለበጎቸው እንደሚሰራ ማወቃቸው ብዙ እምነትና መጽናናትን ይሰጣል። "እግዚአብሔርም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት በነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን" (ሮሜ 8፡28)። አልፎ አልፎ እግዚአብሔር ሰዎችን በታሪክ መድረክ ላይ ካከናወነው በኋላ ስውር ፈቃዱን እንዲረዱት ይፈቅዳል። ኢዮብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተናገራቸው የመጨረሻዎቹ ቃላቶች መካከል እንደተናገረው፡- "ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።" (ኢዮብ 42፡2-3)። በእርግጥም ቅዱሳት መጻሕፍት ኢዮብ ይህን ያህል አስቸጋሪና የሚያሠቃይ መከራ የደረሰበት ለምን እንደሆነ እንዲያውቅ እግዚአብሔር እንደፈቀደ የሚገልጽ አንድም ነገር የለም።

ከስውር ፈቃዱ በተለየ፣ እግዚአብሔር እንድታደርጉ ወይም እንዳታደርጉ የሚፈልጋቸውን ብዙ ነገሮችን ይገልፃል። የእግዚአብሔር የተገለጠው ፈቃድ በዋነኛነት እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዛት ይታያል፣ መለኮታዊ ሕጎች ለምድራዊ ሕልውናህ ግልጽ እና አስተማማኝ መመሪያ ይሰጣሉ። በሰፊው አነጋገር፣ ጌታ የእናንተን መዳን (ክፍል V) እና ለሥነ ምግባር ሕጎቹ መታዘዝን ይፈልጋል። በአሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ተጠቃሏል፣ የእግዚአብሔር የሥነ ምግባር ሕጎች በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይታያሉ (ክፍል VI፣ ምዕራፍ 1)። ከብዙ ምሳሌዎች መካከል አራቱ፡- "ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ ለሚያሳዷችሁም ጸልዩ" (ማቴዎስ 5፡44)፣ "ለሰዎች ሁሉ ይልቁንም ለሚያምኑት መልካም አድርጉ" (ገላትያ 6፡10) ናቸው። "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ከዝሙት እንድትርቁ፥ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ፥ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ" (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡3-4) እና "ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና። መንፈስን አታጥፉ" (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡16-18)። እነዚህ የእግዚአብሔር የተገለጠው ፈቃድ ግልጽ

ምሳሌዎች ናቸው። እንደ ንጉሥ ዳዊት “ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ” (መዝ. 143፡10) በማለት ጸልይ።

<u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ መግለጽ</u>

የዮሴፍን ሕይወት ተመልከት (ከዚህ በፊት በክፍል II፣ ምዕራፍ 3 አንድ ጊዜ ተፈትኗል)። አባቱ ያዕቆብ ከሌሎቹ ልጆቹ ይልቅ ዮሴፍን በግልጽ ይወደው ነበር፤ ይህም ምቀኝነታቸውን አቀጣጠለው። ነገር ግን ደግሞ፣ አስተዋይ ወጣት ሆኖ ሳለ፣ ዮሴፍ የአሥሩን ታላላቅ ወንድሞቹን ክፉ ምግባርና ሲሲግዱለት ያየውን ሕሙንሞን በመናገር አስቆጥቷቸዋል። (ዘፍጥረት 37፡1-11)። ወንድሞቹ ዮሴፍን ሊገድሉት ፈለጉ። (ዘፍጥረት 37፡18-20) በውስጣቸው የቅናት ጥላቻ ነግሷል። ዮሴፍን ለምድያማውያን ነጋዴዎች ወደ ግብፅ ለባርነት ሸጡት። (ዘፍ 37፡25-28፣ 36)። ወንድሞቹ ክህደታቸውን ለመደበቅ ዮሴፍን አውሬ ገድሎ እንደበላው ለአባታቸው ነገሩ። (ዘፍ 37፡31-35)።

በግብፅ ባርነት ውስጥ የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔር ዮሴፍን አጽናንቶ አበለፀገው። (ዘፍጥረት 39፡1-2)። ትጋቱና ታታሪነቱ ግብፃዊው ጌታው ጰጢፋርን የበለጠ ኃላፊነት እንዲሰጠው አደረገው። ዮሴፍ የጲጢፋራን ቤተሰብና እርሻውን ሁሉ ማስተዳደር ቻለ። (ዘፍጥረት 39፡3-6)። ነገር ግን ሁኔታው መሻሻል ሲጀምር የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ልታታልለው ሞከረች። ወጣቱ ባሪያ ልመናዋን ስላልተቀበለ ከፊቷ ሸሸ። ነገር ግን በደረሰባት ተቃውሞ ተናድዳ፣ ሊደፍራት እንደሞከረ በሐሰት ከሰሰችው። በዚህ ምክንያት ጲጥፋራ ዮሴፍን አሳሰረው። (ዘፍ 39፡7-20)።

ሆኖም የእግዚአብሔር መገኘት ከእርሱ ጋር ነበር። ጠባቂው፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ የዮሴፍን ችሎታ ተመልክቶ በሁሉም እስረኞች ላይ ሾመው። በኋላ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃና የዳቦ ጋጋሪዎች አለቃ ላይ ተቆጥቶ ወደዚያው እስር ቤት አስገባቸው። አንድ ቀን ሌሊት ሁለቱም ሕልም አዩና ለዮሴፍ ነገሩት። እግዚአብሔር ትርጉማቸውን ገለጸ፣ እና ዮሴፍ በትዕግሥት ለእያንዳንዱ እውነተኛ ትርጓሜያቸውን ነገራቸው። እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደተናገረው ፈርዖን ዳቦ ጋጋሪውን ሰቅሎ ጠጅ አሳላፊውን ወደ አገልግሎት መለሰው። ጠጅ አሳላፊው ግን ወዲያው ዮሴፍንና ሕልምን የሚተረጉመውን አምላክ ረሳ። (ዘፍጥረት 40፡1-23)።

ከሁለት ዓመት በኋላ ፈርዖን ራሱ በጣም ያስጨነቀው ሁለት ህልሞችን አየ። የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ሕልሙን የፈታለትን ሰው አስታወሰና ለንጉሡ ስለ ዕብራዊው ባሪያ የነገረው። ስለዚህ፣ ፈርዖን ስለራሱ ምስጢራዊ ራእዮች ወጣቱ ዮሴፍን አስጠራው በግብፅ ንጉሥ ፊት ቆሞ ሕልሞቹ ከእግዚአብሔር ለፈርዖን እንደተላኩ ነግሮ ሕልሙን ተረጎመለት። በሕልሞቹ ለሰባት ዓመታት የተትረፈረፈ ምርት እንደሚያገኙ ከዚያም ሰባት ዓመታት ከባድ ረሃብ እንደሚኖር አስቀድሞ አስጠንቅቆት ነበር። ይህም ጥንቃቄ ካልተደረገ በሕዝቡ ላይ ችግር እንደሚደርስ አስረዳው። በመቀጠልም ዮሴፍ ንጉሱ ብልህና አስተዋይ የሆነ ሰው እንዲሾም ነገረው። በተትረፈረፈ አመታት እህል ይሰበስባል እና ያከማቻል እናም በአስቸጋሪው አመታት

ውስጥ በጥንቃቄ ያከፋፍላል። (ዘፍ. 41: 1-36) ፈርዖንም እንዲህ ሲል መለሰ፡- “በውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን እንደዚህ ያለ ሰው እናገኛለንን? ፈርዖንም ዮሴፍን አለው። እንደ አንተ ያለ ብልህ አዋቂም ሰው የለም፥ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሃልና። አንተ በቤቴ ላይ ተሾም፥ ሕዝቤም ሁሉ ለቃልህ ይታዘዝ፤ እኔ በዙፋኔ ብቻ ከአንተ እበልጣለሁ።” በወንድሞቹ የተጠላና ለባርነት የተሸጠው ዮሴፍ አሁን በ30 ዓመቱ ግብፅን በሙሉ ገዛ፣ ከፈርዖን ቀጥሎ ሁለተኛ ገዢ ሆኖ ገዛ። (ዘፍጥረት 41፡39-46)።

እንደተተነበየው የእጥረት ዓመታት የተትረፈረፈ ዓመታትን ተከተሉ። ወደ ከነዓን ስንመለስ የዮሴፍ ቤተሰብ በረሃብ ተሠቃይቷል፤ በግብፅ ብቻ ነበር እህል የተርፈው። ስለዚህም ያዕቆብ አሥር ልጆቹን (ከታናሹ ከብንያም በስተቀር) ከፈርዖን ምግብ እንዲገዙ ላካቸው። (ዘፍ 41፡53-42፡5)። እንደደረሱም በግብፅ ገዥ ባላወቁት ታናሽ ወንድማቸው በዮሴፍ ፊት ሰገዱና እህል እንዲሸጥላቸው ጠየቁት። ዮሴፍ ቢያውቃቸውም ማንነቱን ወዲያውኑ አልገለጸላቸውም። ይልቁንም ወንድሞቹን በስለላ ከሰሳቸው። ክሱን ለማስተባበል ሲፈልጉ ስለቤተሰቦቻቸው ብዙ ማብራሪያ ሰጡ። እና ታናሽ ወንድማቸው ቤት ውስጥ እንዴት እንደቀረ ተናገሩ። ይህ መረጃ የዮሴፍ ወድሞቹ መለወጣቸውን የሚያይበትን ስልት ሆነለት። (ዘፍ 42፡6-16)። ስለዚህ ዮሴፍ ለሦስት ቀን አዘዛቸው። እንዲህም አላቸው “እግዚአብሔርን እፈራለሁና ይህን አድርጉ በሕይወትም ትኖራላችሁ፤ ሐቀኛ ሰዎች ከሆናችሁ ከወንድሞቻችሁ አንዱ በዚህ እስር ቤት ይቀይ ሌሎቻችሁ ለተራቡ ቤተሰቦቻችሁ እህል ውሰዱና ሂዱ። ነገር ግን ቃላችሁ እንዲረጋገጥ እንዳትሞቱም ታናሹን ወንድማችሁን ወደ እኔ አምጡ።” (ዘፍ 42፡17-20)።

ዮሴፍ ወንድሞቹን (ከስምዖን በቀር) የሚበቃ ምግብ ሰጥቶ ለጥቂት ጊዜ ወደ ቤታቸው ላካቸው። ነገር ግን አባታቸው በጣም የሚወደው ትንሹ ልጁ ቢንያም ወደ ግብፅ እንዲሄድ የተባለውን ሐሳብ ተቃወመ። ሆኖም ዘጠኙ ወንድሞች ያለ እሱ ከተመለሱ ምንም ዓይነት እህል መግዛት እንደማይችሉ አጥብቀው ነገሩት። የምግብ አቅርቦቱ እየቀነሰ እና ረሃቡ ሲቀጥል ያዕቆብ በመጨረሻ ተጸጸተ እና ብንያምን ጨምሮ አስር ልጆቹ ወደ ግብፅ አቀኑ። (ዘፍጥረት 42፡25-43፡14)።

በዚህ ሁለተኛ ጉዞ ላይ ዮሴፍ ስምዖንን ፈታ እና ለአሥራ አንዱ ወንድሞች ቤተሰባቸውን በሕይወት ለማቆየት የሚያስችል በቂ ምግብ ሰጣቸው። ይሁን እንጂ ከመሄዳቸው ጥቂት ቀደም ብሎ የራሱን የብር ጽዋ በቢንያም የእህል ከረጢት ውስጥ ደበቀ። ጥቂት መንገድ እንደተጓዙ ዮሴፍ መጋቢውን ላከባቸውና የብር ጽዋው በቢንያም አቁማዳ እንደተገኘ ሲታውቅ ቢንያምን በሌብነት ከሰሳውና ወደ ገዥው ወሰዳቸው። ወንድሞች በግብፅ ገዥ ፊት በድጋሚ በፍርሃት ሲቆሙ ዮሴፍ የተናደደ መስሎ ተናገራቸው። የተጨነቁት ወንድሞች የእርሱ አገልጋዮች እንዲሆኑ ቢያቀርቡም ዮሴፍ ግን ብንያም ብቻ በባርነት እንደሚገዛ ተናገረ። (ዘፍ 44፡1-17)። ይሁዳም ቃል አቀባይ ሆኖ እንዲህ ሲል ለመነ።

> ጌታዬ ሆይ፥ እኔ ባርያህ በጌታዬ ጆሮ አንዲት ቃልን እንድናገር እለምናለሁ፤ እኔንም ባሪያህን አትቆጣኝ፤ አንተ እንደ ፈርዖን ነህና። ጌታዬ ባሪያዎቹን። አባት አላችሁን ወይስ ወንድም? ብሎ ጠየቀ። እኛም ለጌታዬ እንዲህ አልነ። ሽማግሌ አባት አለን፥

ስድስተኛው ልመና እግዚአብሔር ህዝቡን ወደ ፈተና እንዳይመራ ይጠይቃል፣ ይህም አጭር ካቴኪዝም ጌታ ከፈተና እንደሚጠብቃቸው ያስረዳል። ለእንደዚህ አይነት ጥበቃ ለመጸለይ ሶስት መንገዶች አሉ። በመጀመሪያ፣ ስለ ፈተና እንዲያስጠነቅቅህ እግዚአብሔርን ለምኑት። እናንተም በፊናችሁ እነዚህን ሁሉ ማስጠንቀቂያዎች ለማክበር ዓላማ ይኑራችሁ። ቃየን በወንድሙ አቤል ላይ በቀናበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል አስጠንቅቆታል፣ “መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።” (ዘፍጥረት 4፡7)። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ቃየን መለኮታዊውን ምክር ችላ በማለት ምክንያት የመጀመሪያውን ግድያ ፈጽሟል። ሁለተኛ፣ ለፈተና የሚያነሳሳውን ሁሉ ከመንገዳችሁ እንዲያስወግድላችሁ ለምኑት። ለምሳሌ ቅዱሳን “ድህነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ ነገር ግን የዕለት እንጀራዬን ብቻ ስጠኝ” ብለው መጸለይ አለባቸው። “ንዳልጠግብ እንዳልክድህም። እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፤ ድሀም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም፥ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል።” (ምሳሌ 30፡8-9)። በሶስተኛ ደረጃ፣ ከዚህ በፊት የበረታብህ ማንኛውም ነገር የበላይነቱን እንዲያጣ የሚቀድስ ሀይል እንዲሰጥህ ጠይቅ። "በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ... ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።” (ኤፌሶን 6፡10-11, 13)

ነገር ግን ሁሉንም ፈተናዎች ማስወገድ አይቻልም። ስለዚህ ፈተና ሲመጣ ለድጋፍ እና ለመዳን እንጠይቅ፤ እግዚአብሔር እኛን ለመደገፍ፣ ፈተናን መሸከም በምንትችለው ልክ እንዲሆን ገድቦታል። ማለትም ማታለያው ከመንፈሳዊ ጥንካሬህ የበለጠ ደካማ እንዲሆን ሰይጣንን ይገታዋል፤ (ለምሳሌ ኢዮብ 1፡12)፣ ወይም ደግሞ ከመደበኛ መንፈሳዊ ጥንካሬህ በላይ ፈተናን ለመቋቋም እንትችል ጸጋን ይሰጥሃል። ማዳኑንም በተመለከተ እግዚአብሔር ያለ ምንም ነቀፋ ከፈተና ሁሉ የምታመልጡበትን መንገድ ያዘጋጃል። አንዳንድ ጊዜ በእናንተና በፈተናው ምንጭ መካከል ያለውን ርቀት ማስቀመጥን ያካትታል። "ከጎልማሳነት ምኞት ሽሽ" (2ኛ ጢሞቴዎስ 2:22) አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በተለይ መውጣት ሲያቅታችሁ መጸለይን ያካትታል። “ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩም። መንፈስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው” (ማቴ 26፡41)።

መለኮታዊ እርዳታ እያደርገላችሁ አሁንም ለፈተና የምትሸነፉ ከሆነ፣ ለምመጸጸትና ለእውነተኛ ንስሐ ጸልይ። "በኃጢአታችን ብትናዘዙ እርሱ የታመነና ጻድቅ ነው ኃጢአታችንንም ይቅር ይላችኋል ከዓመፃም ሁሉ ያነጻችኋል" (1ኛ ዮሐንስ 1፡9) ንስሐ ስትገቡ በምላሹም እግዚአብሔር በኃጢአታችሁ እንድትኖሩ አይተዋችሁም ወይም ጽኑ ቀጣውን በእናንተ ላይ አይዘረጋም። ይልቁንስ በፍቅር በቅጣት ይመልሳችኋል፡-

> እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር። ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥... ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል። (ዕብ. 12፡5, 11)።

ለማጠቃለል፡- “ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን” ያውቃል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡9)። ከኃጢአት ጋር በምትታገሉበት ጊዜ እርሱ ብዙ ሊረዳችሁ ቃል ገብቷል። እሱ ከአንዳንድ ፈተናዎች ይጠብቃቹሀል እና በሌሎች መካከል ያበረታቹሀል። ነገር ግን ብትሸነፉ ሁሉም ነገር ይጠፋል ማለት አይደለም። ስትጸጸቱ ይቅር ይላል። ንስሐ ባትገቡ ይቀጣቹሀል። በእነዚህ መንገዶች እግዚአብሔር ለገባው ቃል ታማኝ ነው። ፈተናን መቋቋም እንድትችሉ ሁል ጊዜ ይረዳቹሃል፤ በምትሸነፉበት ጊዜም፡- “ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው።” (2ኛ ተሰሎንቄ 3፡3)።

<u>የምርምር ስራ</u>

ታዳጊዎች የሲ.ኤስ. ሉዊስ የስክሪፕት ደብዳቤዎችን ሙሉ በሙሉ እንዲያነቡ ወይም በመጽሐፉ ላይ የተመሰረተ ድራማዊ ትርኢት እንዲመለከቱ ጠይቃቸው። ለእያንዳንዱ ሰው የተወሰነ ፊደል ይምረጡ እና ይመድቡ። ታዳጊዎች የተተሰጡዋቸውን ደብዳቤዎች በጽሁፍ ዘገባቸው ማጠቃለል እና አሁን ባለው የባህል ሁኔታ ውስጥ ያለውን ትርጉም ወይም አስፈላጊነት ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም በያዙት ደብዳቤ ላይ ካለው ፈተና ጋር ያጋጠሟቸውን ተመሳሳይ የሆኑ ፈተናዎችን ይገልጻሉ፤ ነገር ግን እነዚያን ባሒያት በራሳቸው ፈቃድ በመተው ከማንኛውም መጥፎ፣ ጨዋነት የጎደለው ወይም አነጋጋሪ ሁኔታዎች እንዲርቁ ያስጠነቅቋቸዋል።

<u>የቃል ጥቅስ ጥያቄዎች</u>

1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሳቸው ሦስት የፈተና ምንጮች የትኞቹ ናቸው?

ሰይጣን፣ ዓለም እና የእኛን የኃጢአታዊ ተፈጥሮ ናቸው።

2. “ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ። እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?” (ሮሜ 7፡23-24)። “ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።” (ገላትያ 5፡17)። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የትኛው ሐዋርያ ነው ስለ አሮጌው ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ድካም እና ለፈተና የተጋለጠ መሆን ያስተማረው?

ጳውሎስ

3. ለፈተና ምላሽ መስጠት የምንችለው በየትኞቹ አማራጮች ነው?

ለፈተና መሸነፍ እንትችላለን፣ ይህም ኃጢአት ነው። ወይም

ፈተና በመቋቋም እግዚአብሔርን ደስ የመሰኘት እንችላለን።

4. የተፈተነ ግን ኃጢአት ያልሠራ ማን ነው?

ኢየሱስ የተፈተነ ቢሆንም ኃጢአት አልሠራም። "እርሱ በተፈተነ ጊዜ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና" (ዕብ 2፡18)። "ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንምና።" (ዕብ 4፡15)።

5. አንኢት ልጅ ሰይጣን በፈተናት ቁጥር ንስሃ እንደምትገባ ትናገራለች። ምላሻችሁን ከጠየቀች ምን ልትሏት ትችላላችሁ?

ለፈተና እስካልተሸነፈች ድረስ ንስሐ የሚያስፈልገው ኃጢአት እንዳልሆነ ማስረዳት ትችላላችሁ። ሰይጣን ኢየሱስን ስለፈተነው ኢየሱስ ኃጢአት አልሠራም ወይም ንስሐ አልገባም። በዚህ ነጥብ ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ ናቸው፣ (ማቴዎስ 4፡1-11)።

6. ፈተናዎች የተለመዱ ናቸው የሚባለው ለምንድነው?

ፈተናዎች በሁሉም ሰዎች ላይ ደጋግመው ይከሰታሉ። እያንዳንዱ ፈተና ከዚህ በፊት ተከስቷል፤ ለሰው ልጆች አዲስ የሆነ ፈተና የለም።

7. ፈተናንና ውጤቱን እንድትቋቋም የሚረዳህ አምላክ እንዴት ታማኝ ነው?

አንዳንድ ፈተናዎችን እንዳትለማመዱ ይጠብቃቹሃል። ስትፈተኑ ይደግፋችኋል ያዳናችሁማል። በተለይም፣ ከምትችሉት በላይ ፈተናን አይፈቅድም፣ እና ከፈተና ሁሉ የምታመልጡበትን መንገድ ያዘጋጅላቹሃል። በፈተና ወድቃችሁ ንስሃ ስትገቡ ይቅር ይላችኋል። ንስሐ ካልገባችሁ በፍቅር ይቀጣችኋል እናም በዚህ ይበልጥ በሚያሳምም መንገድ ያድሳችኋል።

8. "ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና" (ሉቃስ 22፡31-32)። ኢየሱስ ስለሚመጣው ፈተና ያስጠነቀቀው በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የትኛውን ሐዋርያ ነው?

ስምዖን ጴጥሮስ

9. በዘፍጥረት 39፡10 ዮሴፍ ከፈተና እንዴት አመለጠ?

"ይህንም ነገር በየዕለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር፤ እርሱም ከእርስዋ ጋር ይተኛ ዘንድ ከእርስዋም ጋር ይሆን ዘንድ አልሰማትም። እንዲህም ሆነ፤ በዚያን ጊዜ ሥራውን እንዲሠራ፤ ወደ ቤቱ ገባ፤ በቤትም ውስጥ ከቤት ሰዎች ማንም አልነበረም። ከእኔ ጋር ተኛ ስትል ልብሱን ተጠማጥማ ያዘችው፤ እርሱም ልብሱን በእጅዋ ትቶላት ሸሸ" (ዘፍ 39፡10)።

10. በሚቀጥሉት ጥቅሶች ላይ በመመስረት መንፈሳዊ ጥንካሬያችሁንን ለመጨመር አሁን ምን ማድረግ ትችላላችሁ። ከዚህ በኋላ ፈተና ሲከሰት እንዴት መቋቋም ትችላላችሁ?

ሀ. "አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ" (መዝሙረ ዳዊት 119:11)

በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ በማሰላሰል እና ቁልፍ ጥቅሶችን በቃል በመያዝ።

ለ. “እኔ ግን እግሮቼ ሊሰናከሉ፥ አረማመዴም ሊወድቅ ትንሽ ቀረ። የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና።” (መዝ. 73፡2-3)።

በእግዚአብሔር ባብቃ እርካታን ማግኘት በመማር፣ እና ባለመመኘት።

ሐ. “በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር” (ኤፌሶን 3፡16)።

በተለይ ፈተናን በመቃወም ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል መጸለይ።

መ. “እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ። ዲያብሎስን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል” (ያዕቆብ 4፡7)።

በሕይወታችሁ ያለውን ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር አስረክቡ—ሁሉም ግቦቻችሁ፣ ሀብቶቻችሁ፣ አስተሳሰቦቻችሁ፣ አመለካከቶቻችሁ እና ድርጊቶቻችሁ። ፈተና ሲመጣ ሰይጣንን ተቃወሙ; ማለትም ጸንታችሁ ቁሙ፥ ጸጋን ለማግኘት እግዚአብሔርን ለምኑ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፡ እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ማድረግ

የጌታ ጸሎት መደምደሚያ ሦስት ነገሮችን ያስተምራል። በመጀመሪያ ለሚያስፈልጉችሁ ነገሮች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ብቻ ጸልዩ። ሁለተኛ፣ ልመናዎችን የመስማት ሥልጣን ያለው፣ ጥያቄዎቻችሁን የሚፈጽምና ፍላጎቶቻችሁን የሚያሟላ እርሱ ነውና እርሱን አመስግኑ። ሦስተኛ ጸሎትን እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ እርግጠኛ ሁኑ።

<u>እግዚአብሔርን ብቻ ፈልጉ</u>

አንዳንድ ሰዎች ጸሎት የተረጋጋ መንፈስን ስለሚያዳብር ወይም አርኪ ስሜታዊ ወይም ሃይማኖታዊ ተሞክሮ ስለሚሰጥ ጸሎት ጥሩ እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል። ጥብቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዞችን ችላ ቢልም እንኳ ጸሎት ጠቃሚ እንደሆነ አድርገው

ይቆጥሩታል። ለእነሱ ለማን መጸለይ እንዳለበት እንኳ ምናቸውም ላይሆን ይችላል። በሌላኛው ጫፍ ማንም ሰው በትክክል ቢሰማም ባይሰማም ውይይቱ አስፈላጊ ነው።

ግን ምን ትላለህ? ለማንስ ብትጸልይ ለውጥ አለው? ለምን ወደ አላህ፣ ቡድሃ፣ እናት ምድር፣ ዓለም አቀፋዊ መርሆ፣ የሕይወት ኃይል፣ የሞቱ ቅዱሳን፣ የሞቱ አባቶች፣ ሃይማኖታዊ ምስል ወይም የጓሮ አጥር ቢሆን ለምን አትጸልዩም? ምናልባት "ምንም አይጠቅምም" ትሉ ይሆናል። ለምን አይሆንም? "መርዳት አይችሉም" ብላችሁ ምላሽ ልትሰጡ ትችላላችሁ። በአንጻሩ የቅዱሳት መጻሕፍቱ እግዚአብሄር አምላክ ያስባል፣ ይሰማል፣ ምላሽ ይሰጣል፣ እና ይረዳል የሚለውን ይቃወማል። ዓመፀኛው ሕዝብ ታማኝነቱን ሲያጣ ጌታ ይህንን ለይሁዳ ተናግሯል፡-

> በማን ትመስሉኛላችሁ? ከማንስ ጋር ታስተካክሉኛላችሁ? እንመሳሰል ዘንድ ከማን ጋር ታስተያዩኛላችሁ? ወርቁን ከኮረጆ የሚያፈስሱ ብሩንም በሚዛን የሚመዝኑ እነርሱ አንጥረኛውን ይቀጥራሉ፥ እርሱም አምላክ አድርጎ ይሠራ ዋል፤ ለዚያም ይጐነበሱለታል ይሰግዱለትማል። በጫንቃቸው ላይ አንሥተው ይሸከሙታል በስፍራውም ያደርጉታል፥ በዚያም ይቆማል፥ ከስፍራውም ፈቀቅ አይልም፤ ሰውም ወደ እርሱ ቢጮኽ አይሰማውም ከመከራውም አያድነውም። ይህን አስቡና አልቅሱ፤ ተላላፊዎች ሆይ፥ ንስሐ ግቡ፥ ልባችሁንም መልሱ። እኔ አምላክ ነኝና፥ ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም። በመጀመሪያ መጨረሻውን፥ ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ፤ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ እላለሁ (ኢሳ 46፡5-10)።

አንዳንድ ጊዜ ጌታ ጸሎትን በታላቅ ጥበብ ስለሚመልስ ማንም ምን እንደተፈጠረ እና ማን እንዳደረገው ትይታወቅም። በአንድ ወቅት ነቢዩ ኤልያስ ክፉውን ንጉሥ አክዓብን 450 የበኣል ነቢያቱንና 400 የአሼራን (Asherah) ነቢያትን ጠራ። በሺዎች የሚቆጠሩ የማወቅ ጉጉት ያላቸው ተመልካቾችም በትዕይንቱ ላይ ተገኝተዋል። የተቀጠረው ጊዜ ሲደርስ ነቢያቱ በአገሪቱ የሕይወት ወይም የሞት ትግል ለመካፈል በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተሰበሰቡ። ኤልያስ ለተራው ሕዝብ እንዲህ አለ፣ "እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ።" (1ኛ ነገ 18፡21)። የጌታ ብቸኛ ሻምፒዮን ጦሩን ከጣለ በኋላ በእስራኤል ውስጥ በጣም ተወዳጅ ከሆኑት የሁለቱ የሐሰት አማልክት 850 ታዋቂ ነቢያት ጋር ተጋፈጠ። ነገር ግን፣ አንዳንዶች እንደሚሉት፣ አንድ ሰው ሲደመር እግዚአብሔር የበለጠ ነገር ያደርጋል፣ እናም የዕለቱ ክስተቶች ይህን አረጋግጠዋል።

ኤልያስ እስራኤላውያን ሊከተሉት የሚገባውን እውነተኛ አምላክ ለማወቅ የሚያስችል አስደናቂ ውድድር አቀረበ። ለ450ዎቹ የበኣል ነቢያት አንድ ወይፈን እንዲቆራርጡና በመሠዊያው እንጨት ላይ እሳት ሳይጨምሩ እንዲያስቀምጡ ነገራቸው። ኤልያስ እኔም እንዲሁ አደርጋለሁ አለ። "የአምላካችሁን [በኣልን] ስም ጥሩ፤ እኔም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ። በእሳት የሚመልስ እርሱ አምላክ ይሁን" አለ። (1ኛ ነገ 18፡24)። ተመልካቾቹ እነዚህን ውሎች ያዙ፣ እና ኤልያስ ተቃዋሚዎቹ እንዲቀድሙ ፈቀደላቸው።

> ወይፈኑንም ወስደው አዘጋጁ፥ ከጠዋትም እስከ ቀትር ድረስ። በኣል ሆይ፥ ስማን እያሉ የበኣልን ስም ጠሩ። ድምፅም አልነበረም፥ የሚመልስም አልነበረም፤ በሠሩትም መሠዊያ ዙሪያ እያነከሱ ያሸበሽቡ ነበር። በቀትርም ጊዜ ኤልያስ። አምላክ ነውና በታላቅ ቃል ጩኹ፤ ምናልባት አሳብ ይዞታል፥ ወይም ፈቀቅ ብሎአል፥ ወይም ወደ መንገድ ሄዶአል፥ ወይም ተኝቶ እንደ ሆነ መቀስቀስ ያስፈልገዋል እያለ አላገጠባቸው። በታላቅም ቃል ይጮኹ፥ እንደ ልማዳቸውም ደማቸው እስኪፈስስ ድረስ ገላቸውን በካራና በቀጭኔ ይብዋጭሩ ነበር። ቀትርም ካለፈ በኋላ መሥዋዕተ ሠርክ እስኪደርስ ትንቢት ይናገሩ ነበር፤ ድምፅም አልነበረም፥ የሚመልስና የሚያደምጥም አልነበረም። (1 ነገ. 18: 26-29).

ከዚህ በኋላ ኤልያስ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ወደ ሁለተኛ መሠዊያ ቀረበ።በዚህ መሠዊያ በአንድ ወቅት ለእውነተኛ እና ለሕያው አምላክ መባ ይቀርብ ነበር፣ ነገር ግን መሠዊያው ከብዙ ዓመታት በቸልተኝነት ጥቅም ላይ ከለመዋሉ የተነሳ ፈርሷል። የእስራኤልን ነገዶች የሚወክሉ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን ወስዶ መሠዊያውን መልሶ ሠራ፣ በዙሪያውም ጉድጓድ ቆፈረ፣ እንጨቱንና መሥዋዕቱን አስተካክሎ ረበረበ። ኤልያስ አገልጋዮቹን አንድ ጊዜ ሳይሆን ሦስት ጊዜ በመሠዊያው ላይ አራት ትላልቅ ውኃ የሞሉ ጋኖች በተረበረበው እንጨት ላይ እንዲደፉ አዘዘ። ውሃውም ጉድጓዱን ሞላው። ከዚያም፣ መሥዋዕተ ሰርክ በደረሰ ጊዜ ኤልያስ ሁሉም ሰው እያየ ወደ ፊት ወጥቶ ጸለየ።

> መሥዋዕተ ሠርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነቢዩ ኤልያስ ቀርቦ። አቤቱ፥ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፥ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ፥ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ፥ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ። አንተ፥ አቤቱ፥ አምላክ እንደ ሆንህ፥ ልባቸውንም ደግሞ እንደ መለስህ ይህ ሕዝብ ያውቅ ዘንድ ስማኝ፥ አቤቱ፥ ስማኝ አለ። (1ኛ ነገ 18፡36-37)።

ወዲያውም እሳት በመሠዊያው ላይ ወረደ፣ እንጨቱን እና መሥዋዕቱን በላ። አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች እና በዙሪያው ያሉትን አፈር አቃጠለ እና በጉድጓዱ ውስጥ ያለውን ውሃ ላሰ። እግዚአብሔር ለኤልያስ ጸሎት በቀጥታ ምላሽ የሰጠው አስደናቂ ትርኢት ተመልካቾቹን አስደነገጣቸው። ከእውነተኛው አምላክ በቀር ማን እንዲህ ያለ ነገር ሊያደርግ ይችላል? ከሰማይ የወረደው እሳት እግዚአብሔር ብቻ ጌታ መሆኑ ሁሉንም አሳመነ።

ታዲያ ለምን በቅዱሳት መጻሕፍት ወደተገለጠ አምላክ ብቻ መጸለይ አለብን? በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ሁነው የሆነውን ላዩት መልሱ ግልጽ ነበር። ከበኣል በተለየ መልኩ ኤልያስ የተከተለው አምላክ ጸሎትን ሰምቶ የሚመልስ ብቸኛው አምላክ ነበር።

<u>እግዚአብሔርን በትክክል ተመልከት</u>

ጸሎት ልመናዎችን ከማቅረብ የበለጠ ነገርን ይይዛል። መንግሥትን፣ ኃይልንና ክብርን ለዘለዓለም እግዚአብሔር እየሰጠ እሱን ያመሰግናል። እነዚህን እውነቶች ማስታወስ በጸሎት ጊዜ ብዙ ብርታትን ይሰጣል። እነዚህ ነገሮች የጌታ ስለሆኑ፣ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ስልጣን፣ ችሎታ እና ጸሎትን የመስማት እና የመቀበል ፍላጎት ላይ በመተማመን ወደ ጸጋው ዙፋን መቅረብ ይችላሉ። እነዚህን ሦስት እውነቶች አንድ በአንድ እንመልከት፡-

ሀ. እሱ ሉዓላዊ ንጉሥ ስለሆነ ሥልጣን አለው– የሱ ንግስና በአንድ ግዛት፣ በመላው ምድር፣ ወይም በአጽናፈ ሰማይ ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ነገር ላይ ንጉሥ ነው። “ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ፥ ያሳያል።” (1ጢሞ. 6፡15)። ሁሉን ስለፈጠረ እና የተመረጡትን ስለተቤገር፣ የሁሉ ነገር ባለቤት ነው እናም ማንኛውንም ነገር ለህዝቡ መስጠት ይችላል። የማዘዝ እና የመግዛት ከፍተኛ ስልጣን አለው። "ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው። የዘመናት ንጉሥ ሆይ፣ መንገድህ ጻድቅና እውነት ነው” (ራዕይ 15፡3) ብቻውን ልመናዎችን የመስማት ስልጣን ላለው ወደዚህ ታላቅ፣ ግርማ ሞገስ ያለው የንጉሶች ንጉስ ጸልዩ።

ለ. እግዚአብሔር ማለቂያ የሌለውን ኃይል ይጠቀማል። “አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ ታላቅ አምላክ ኃያልና የሚያስፈራም ነውና” (ዘዳ 10፡17)። ለምንድነው አንድን ነገር ለመስጠት አቅም ከሌለው ሰው ወይም ከአንድ ነገር የማንጠይቀው? ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ሁሉንም ነገር ማድረግ ስለሚችል መጠየቅ ያለብን እሱን ነው። ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ምንም የሚከብድ ነገር የለም። ብርቱ ክንዱን ዘርግቶ በኃይለኛ እጁ ተአምራትን ያደርጋል።

በሚስጥራዊ ልምምድ፣ በባዕድ አምልኮ ሥርዓት ወይም በማህበረሰብ ልምድ መጸለይ ዋጋ ቢስ እና ትርጉም የለሽ ነው። በምትኩ፣ ወደ ከበረው፣ ሁሉን ቻይ ንጉሥ እጸልይ። መስጠት የሚችልውንና ልመናችንን ለመመለስ የሚፈልገውን ብቻ ለመስማት ፈቃደኛ እንሁን፣ ። እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንደዚህ ነው, እና ሁልጊዜም ይሆናል፡ “መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ነው፣ ግዛቱም ለልጅ ልጅ ነው” (መዝ. 145፡13)። ወደ ሌላ ሰው ወይም ነገር መጸለይ እግዚአብሔርን ያዋርዳል፣ ዘላለማዊ መንግሥቱን፣ ኃይሉን እና ክብሩን ያቃልላል።

<u>ጸሎትን በትክክል ጨርስ</u>

በጋራ ጸሎት “አሜን” በሚለው ቃል የሚደመደመው ለምን እንደሆነ አስበህ ታውቃለህ? ሥርዓት ስለሆነ ብቻ ነውን? መጽሃፎች እና ፊልሞች ብዙውን ጊዜ "ተፈጸመ" በሚሉት ቃላት እንደሚዘጉ ሁሉ ጸሎት ማለቁን ሁሉም ሰው እንዲያውቅ ነውን? ወይም የጽሑፍ መልእክት በሚላክበት ጊዜ የመላኪያ ቁልፍን እንደመጫን ነውን? ወይስ እግዚአብሔር ጸሎቱን የሚሰማው የሚጸልየው ሰው “አሜን” ካለ ብቻ ነውን?

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ 50 ጊዜ ያህል የተገለጸው “አሜን” የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ ልመናዎችን በማመልከት “እንዲህ ይሁን” እና “አዎ ይሁን” የሚል ፍቺ አለው። እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ እና ፍፁም በሆነ መንገድ መልስ እንደሚሰጥ ጥልቅ የሆነ ትህትናና ፍላጎትን ይገልጻል። “እባክህን እነዚህን የጠየቅኳቸውን ነገሮች ስጠኝ (ማለትም፣ እንደዚያ ይሁን) እንደማለት ነው። እኔ ለፈቃድህ የተሰጠሁ በምሆንበት መሰረት እንደምትመልስ አውቃለሁ (ማለትም ይሁን)።” ውዳሴንና ሌሎች እውነቶችን ሲጸለዩ ወይም ሲዘመሩ የሚነገሩትን እውነታዎች በተመለከተ “አሜን” ማለት ደግሞ “እውነት ነው” ማለት ነው። “እነዚህ ነገሮች እውነት ናቸው” የሚለውን ያሳያል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ያቀረበውን ጸሎት ተመልከት፡-

> ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ። እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን። (ኤፌ 3፡14-21)።

አሜን የሚለው እግዚአብሔር የጳውሎስን ልመና እንደይሰማ መሻቱን ይገልፃል (እንደዚያ ይሁን) እና ጌታ ጸሎቱን ላንደሚመልስ መተማመኑን ይገልጻል። በተጨማሪም አሜን የአብ ክብር በክርስቶስ ኢየሱስ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደሚበራ እና ለዘላለም እንዲሁ እንደሚሆን ማመኑን ያሳያል። (ይህ እውነት ነው) ማለት ነው። “በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለእግዚአብሔር ክብር” ‘አሜን’ ይባላል። (2ኛ ቆሮንቶስ 1፡20)።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጥያቄዎች</u>

1. የጌታ ጸሎት መደምደሚያ ምን ሦስት ነገሮችን ያስተምራል?

   ሰዎች ወደ ሕያውና እውነተኛው አምላክ እንጂ ወደ ሌላ ሰው ወይም ነገር መጸለይ የለባቸውም።

   ልመናዎችን የመስማት፣ ጥያቄዎችን የመመለስ ሃይል እና ፍላጎቶችን የማሟላት ፍላጎት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

   እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ጸሎትን ይሰማል፤ መልስም ይሰጣል።

2. የበኣል ነቢያት ያላደረጉት ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ምን አደረገ?

ኤልያስ እግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ውኃ እንዲደረግ አዘዘ፤ ነገር ግን በበኣል መሠዊያ ላይ ምንም ውኃ አልተደረገም። በተጨማሪም ኤልያስ በኣል ወደ ተባለው የሐሰት አምላክ ሳይሆን ወደ ሕያውና እውነተኛ አምላክ ጸለየ።

3. የጌታ ጸሎት በምትጸልይበት ጊዜ ስለእግዚአብሔር የምትንናገራቸው የትኞቹን ሦስት ነገሮች ነው?

መንግሥት፣ ኃይልና ክብር

4. የእግዚአብሔር መንግሥት ከጸሎት ጋር ምን አገናኘው?

ታላቁ የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር ሁሉንም ይገዛል። ልመናዎችን የመስማት ስልጣን አለው።

5. የእግዚአብሔር ኃይል ከጸሎት ጋር ምን አገናኘው?

ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር የማድረግ ችሎታ አለው። የማንኛውንም ልመና መልስ ማቅረብ ይችላል።

6. የእግዚአብሔር ክብር ከጸሎት ጋር ምን አገናኘው?

ክብሩን ስለሚያሳይ እግዚአብሔር የህዝቡን ልመና ሊመልስ ይወዳል።

7. ንጉስ ዳዊት፡ "አቤቱ፥ የአባታችን የእስራኤል አምላክ ሆይ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ተባረክ። አቤቱ፥ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል፥ ክብርም፥ ድልና ግርማ ለአንተ ነው፤ አቤቱ፥ መንግሥት የአንተ ነው፥ አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ። ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው፥ አንተም ሁሉን ትገዛለህ፤ ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው፤ ታላቅ ለማድረግ፥ ለሁሉም ኃይልን ለመስጠት በእጅህ ነው። አሁንም እንግዲህ፥ አምላካችን ሆይ፥ እንገዛልሃለን፥ ለክቡር ስምህም ምስጋና እናቀርባለን።" (1ኛ ዜና 29፡10-13)። የጌታ ጸሎት መደምደሚያ መንግሥት፣ ኃይልና ክብር የእግዚአብሔር እንደሆነ ይመሰክራል። ዳዊት ያጸለየው ከእነዚህ ከሦስቱ ነገሮች መካከል የትኛውን ነው?

ሀ. ዳዊት መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ሰጠው። "አቤቱ፥ መንግሥት ያንተ ና፤ አንተ በሁሉም ላይ ራስ ሆነህ ከፍ ከፍ አለህ። አንተ የሁሉም ነገር ገዥ ነህ።"

ለ. ዳዊት ኃይሉን ለእግዚአብሔር ሰጠው። "ጌታ ሆይ፣ ታላቅነትና ኃይል የአንተ ነው... . ከፍ ከፍ ለማድረግ እና ለሁሉም ኃይልን ለመስጠት ኃይልና ኃይል በእጅህ አለ።

ሐ. ዳዊት ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ። "ክብር እና ግርማ ሞገስ...አቤቱ የአንተ ነው... . አሁን፣ አምላካችን፣ እኛ... የከበረ ስምህን እናከብራለን።

8. ልመናን በተመለከተ “አሜን” ማለት ምን ማለት ነው?

“እንዲህ ይሁን” እና “እንዲያ ይሁን” ማለት ነው። እነዚህ ሀረጎች እግዚአብሔር እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ እንደሚታመን ያሳያሉ።

8. ውዳሴን በተመለከተ “አሜን” ማለት ምን ማለት ነው?

“በእውነት” ወይም “ይህ እውነት ነው” ማለት ነው።

በመጨአሻም ከነዚህ መዝሙሮች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ዘምሩ። በአማራጭ፣ እንደ የመደምደሚያ ጸሎት ለማንበብ አንድ መዝሙር ይምረጡ።

1. “ምስጋና ሁሉ በላይ የሚገዛ አምላክ ይሁን”
2. “ከሰማይ በታች ከሚኖሩት ሁሉ”
3. “ለአምላካችን የማይሞት ምስጋና ስጡ”
4. “አንተ ታላቅ ይሖዋ ሆይ ምራኝ”
5. "አሁን አምላካችን እግዚአብሔር ይባረክ"
6. “ፈተና አትውሰዱ”

ክፈል IX
የጌታ ጸሎት

ተጨማሪ መግለጫ

የታዳጊዎች የስራ ሉኮች

ምዕራፍ 1፡ የእግዚአብሔር አቀራረብ እና ክብር _____72

ምዕራፍ 2፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እና ፈቃድ _____81

ምዕራፍ 3፡ የእግዚአብሔር አቅርቦት እና ምሕረት _____95

ምዕራፍ 4፡ የእግዚአብሔር ማዳን እና ልቀት_____105

ክፍል IX: የጌታ ጸሎት

ምዕራፍ 1፡ የእግዚአብሔር አቀራረብ እና ክብር

ካቴኪዝም

ጥ. የጌታ ጸሎት መቅድም ምን ያስተምረናል?

መ. የጌታ ጸሎት መቅድም፣ እርሱም፣ በሰማያት የምትኖር አባታችን፣ እኛን ለመርዳት የሚችል እና ዝግጁ የሆነ አባት ልጆች እንደመሆናችን መጠን በፍጹም አክብሮትና እምነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ከሌሎች ጋር እና ለሌሎች መጸለይ እንዳለብን ያስተምረናል።

ጥ. በመጀመሪያው ልመና የምንጸልየው ስለ ምንድነው?

መ. በመጀመሪያው ልመና ማለትም፣ "ስምህ ይቀደስ" በሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ለእኛና ለሌሎች እራሱን በሚገልጥበት ነገር ሁሉ እሱን ለማክበርና ሁሉንም ነገር ለርሱ ክብር እንሆን እንጸልያለን።

<u>ስያሜዎችን ግለጹ</u>

መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ታዳጊዎች ከታች የተዘረዘሩትን ቃላት ትርጉም እንዲፈልጉ ጠይቃቸው፡ የእያንዳንዱን ፍች እንዲያነቡና ከዚያም የተጻፈውን ፍቺ ሳያዩ ቃሉን በራሳቸው አባባል ለመተርጎም ይሞክሩ። እያንዳንዱን ቃል በደንብ እስኪረዱት ድረስ ትርጉሙን በማንበብ እና በራሳቸው አባባል በየተራ እንዲገልጹ ንገራቸው። የተጻፈውን ፍች በእያንዳንዱ ጊዜ በቀላሉ የሚደጋግሙ ከሆነ በመጀመሪያ የሁሉንም ቃላት ፍችዎች እንዲያነቡ ምራቸው፤ ከዚያም ሳያዩ የሁሉንም ቃላት ፍች በራሳቸው አባባል ይግለጹ። በመቀጠል፣ የካቴኪዝም ጥያቄዎችንና መልሶቻቸውን እንደገና ካነበቡ በኋላ፣ ስለ መቅድም እና የመጀመሪያ ልመና የቻሉትን ያህል በራሳቸው አባባል እንዲያብራሩ ጠይቃቸው።

መቅድም

ክብር

ልመና

የተቀደሰ

<u>እንደገና በቀላሉ መፃፍ</u>

በተሻለ ግንዛቤ ላይ በመመስረት ካቴኪዝምን በራሳችሁ አባባል እንደገና ፃፉ

ጥ.

መ.

ጥ.

መ.

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ</u>

እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚደግፈውን የካቴኪዝም ሐረግ(ዎች) ለዩ።

መዝሙረ ዳዊት 72:19 የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘላለም ይባረክ፤ ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይምላ። ይሁን፤ ይሁን።

የሐዋርያት ሥራ 12:5፣ ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።

ሮሜ 8፡15 እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ።

ሮሜ 11፡36 ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

ኤፌሶን 3፡12፣ በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን።

ያዕቆብ 4፡8 ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ።

1ኛ ዮሐ 3፡1 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።

<u>የካቴኪዝም ጥያቄዎች</u>

1. መቅድም ምንድን ነው?

2. በምትጸልይበት ጊዜ ወደ እግዚአብሄር መቅረብ ያለብህ በምን ዓይነት አመለካከት ወይም እይታ ነው?

3. በጌታ ጸሎት ውስጥ ከሌሎች ጋር እንድትጸልይ የሚያስተምር የትኛው የተውላጠስም ገላጭ የያዘ ቃል ነው? **(አባታችን)**

4. በጌታ ጸሎት መግቢያ ውስጥ እግዚአብሔርን እንድንፈራ የሚያስታውስ የትኛው አባባል ነው?

5. በመግቢያው ላይ የሚገኝና እግዚአብሔር በሰማይ ቢሆንም በጸሎት ወደ እርሱ መቅረብ እንደምትችል የሚያስታውስ የትኛው አባባል ነው?

6. በዮሐንስ 1፡12 መሰረት እውነተኛና ሕያው እግዚአብሔርን አባታቸው ብሎ የመጥራት መብት ያለው ማን ነው?

7. አጭሩ ካቴኪዝም ቁጥር 1 "የሰው ልጅ ዋና ፍጻሜ እግዚአብሔርን ማክበር ነው" ይላል። አጭር ካቴኪዝም #101 እንደሚያብራራው ይህ መግለጫ ከጌታ ጸሎት የመጀመሪያ ልመና ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

የቃል ጥቅስ

ዕብራውያን 4፡16 “እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።”

1 “እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።” (ዕብ. 4፡14)። በዚህ ጥቅስ መሰረት በቃል ጥቅሱ ውስጥ ያሉት "እኛ" የሚለውን ተውላጠስም የሚያመለክተው እነማንን ነው?

2. ጓደኛህ እንዲህ አለ፡- “ከባድ ችግር ውስጥ ስገባ በሰማይ ላለው ትልቅ ሰው እጸልያለሁ፣ እሱም አንዳንድ ጊዜ ይረዳኛል ።” ይህ አባባል ከጌታ ጸሎት ጋር ይስማማል?

3. በምትጸልይበት ጊዜ ወደ እግዚአብሄር መቅረብ ያለብህ በምን ዓይነት ዝንባሌ ነው?

4. “በድፍረት” መጸለይ ሲባል ምን ማለት ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፦ የእግዚአብሄርን ስም መቀደስ

1. “ቅዱስ” ማለት ምን ማለት ነው?

2. “ማክበር” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጡ አንዳንድ ቃላት አነማንን ናቸው?

3. “ቅዱስ”ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጡ አንዳንድ ቃላት አነማንን ናቸው?

4. “ስምህ” የሚለው ምንን ያመለክታል?

5. የእግዚአብሄርን ስም መቀደስ ሲባል ምን ማለት ነው?

6. አቤቱ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፥ እንደ ሥራህም ያለ የለም። ያደረግሃቸው አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ፥ አቤቱ፥ በፊትህም ይሰግዳሉ፥ ስምህንም ያከብራሉ፤ አቤቱ፥ ድንቅ የምታደርግ አንተ ታላቅ ነህና፥ አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና። (መዝ. 86፡8-10)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ዘማሪው የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ መሆኑን የሚያሳዩት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

7. የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር አምጡ፥ ክብርንና ኃይልን ለእግዚአብሔር አምጡ።

29 ፤ ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ፤ ቍርባንን ይዛችሁ በፊቱ ግቡ፤ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ። (1ኛ ዜና 16፡28-29)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ዘማሪው የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ መሆኑን የሚያሳዩት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

8. “ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ” (ራዕይ 15፡4)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ዘማሪው የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ መሆኑን የሚያሳዩት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

ክፍል IX: የጌታ ጸሎት

ምዕራፍ 2፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እና ፈቃድ

ካቴኪዝም

ጥ. በሁለተኛው ልመና ውስጥ ስለ ምን እንጸልያለን?

ሀ. በሁለተኛው ልመና፣ ማለትም፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ የሰይጣን መንግሥት እንድትፈርስ እንጸልያለን። እና የጸጋው መንግሥት እንዲራመድ, እኛ ራሳችን እና ሌሎች ወደ እርስዋ አምጥተው እና በውስጡ እንዲቆዩ; የክብር መንግሥትም ትፈጥን ዘንድ።

ጥ. በሶስተኛው አቤቱታ ውስጥ ስለ ምን እንጸልያለን?

ሀ. በሦስተኛው ልመና፣ እርሱም፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች በምድርም ትሁን፣ እግዚአብሔር በጸጋው፣ ፈቃዱን እንድናውቅ፣ እንድንታዘዝ እና በሁሉም ነገር እንድንገዛ እንድንችል ፈቃደኞች እንድንሆን እንጸልያለን። መላእክት በሰማይ እንደሚያደርጉት ነገሮች።

<u>ስያሜዎችን ግለጹ</u>

መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ታዳጊዎች ከታች የተዘረዘሩትን ቃላት ትርጉም እንዲፈልጉ ጠይቃቸው፡ የእያንዳንዱን ፍች እንዲያነቡና ከዚያም የተጻፈውን ፍቺ ሳያዩ ቃሉን በራሳቸው አባባል ለመተርጎም ይሞክሩ። እያንዳንዱን ቃል በደንብ እስኪረዱት ድረስ ትርጉሙን በማንበብ እና በራሳቸው አባባል በየተራ እንዲገልጹ ንገራቸው። የተጻፈውን ፍች በእያንዳንዱ ጊዜ በቀላሉ የሚደጋግሙ ከሆነ በመጀመሪያ የሁሉንም ቃላት ፍችዎች እንዲያነቡ ምራቸው፤ ከዚያም ሳያዩ የሁሉንም ቃላት ፍች በራሳቸው አባባል ይግለጹ። በመቀጠል፣ የካቴኪዝም ጥያቄዎችን እና መልሶችን እንደገና አንብበው ስለ ሁለተኛው እና ሦስተኛው ልመናዎች በተቻላቸው መጠን በራሳቸው አባባል ያብራሩ።

መንግሥት

ጸጋ

የላቀ

ክብር

ፈቃድ

<u>በቀላል መንገድ እንደገና ጻፉ</u>

በተሻለ ግንዛቤ ላይ በመመስረት ካቴኪዝምን በራሳችሁ አባባል ፃፉ።።

ቃላቶች.

ጥ.

መ.

ጥ.

መ.

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ</u>

እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚደግፈውን የካቴኪዝም ሐረግ(ዎች) ለዩ።

መዝሙረ ዳዊት 67:1-2 “እግዚአብሔር ይማረን ይባርከንም፥ ፊቱንም በላያችን ያብራ፤ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ማዳንህን፥ መንገድህንም በምድር እናውቅ ዘንድ።

መዝሙረ ዳዊት 68፡1 "እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ። ጠላቶቹ ከፊቱ ይሸሹ።

መዝሙረ ዳዊት 103:20 ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።

መዝሙረ ዳዊት 119:33-36 አቤቱ፥ የሥርዓትህን መንገድ አስተምረኝ፥ ሁልጊዜም እፈልገዋለሁ። እንዳስተውል አድርገኝ፥ ሕግህንም እፈልጋለሁ፤ በፍጹም ልቤም እጠብቀዋለሁ። እርስዋን ወድጃለሁና የትእዛዝህን መንገድ ምራኝ። ልቤን ወደ ምስክርህ አዘንብል፥ ወደ ስስትም አይሁን።

ሮሜ 10:1፣ ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው።

ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 2፡13 ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡1 “በመጨረሻም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል በቶሎ እንዲሰማና በእናንተ ዘንድ እንደነበረው ክብርም እንዲሆን ጸልዩልን።

የዮሐንስ ራእይ 22፡20 ይህን የሚመሰክር። አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።

<u>የካቴኪዝም ጥያቄዎች</u>

1. ሁለተኛው ልመና የሚያመለክተው ስለ የትኞቹ ሦስት መንግሥታት ነው?

2. ስለ እያንዳንዱ መንግሥት ምን መጸለይ አለችሁ?

3. በህይወታችሁ ውስጥ ሁነቶችን እና ውሳኔዎችን እንዲቆጣጠር መጸለይ ያለባችሁ ወደ ማን ነው?

4. የራሳችሁን ፈቃድ እንድትተዉ እና በምትኩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድትፈልጉ የሚያደርጋችሁ ምንድን ነው?

5. ለሚከተለው ችሎታ እና ፈቃደኝነት እንዲኖራችሁ መጸለይ የምትችሉት እንዴት ነው፡-

ሀ. በሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ?

ለ. በሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመታዘዝ?

ሐ. በሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመገዛት?

6. በመዝሙር 103:20 መሠረት በሰማይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚታዘዙ እነማን ናቸው?

ተቃል ጥቅስ

የሐዋርያት ሥራ 26፡18 የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።

1. የስለ ይጣንን መንግሥት አስብ፡-

ሀ. “ዓለም ሁሉ በክፉው ቁጥጥር ሥር ነው” (1ኛ ዮሐንስ 5፡19)። ሰይጣን መንግሥት የት ነው ያለው?

ለ. ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ (ሮሜ 5:12) አንድ ሰው እንዴት ወደ ሰይጣን መንግሥት ይገባል?

ሐ. በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። (ኤፌሶን 2፡2)። የሰይጣንን መንግሥት የሚያገለግለው ማን ነው?

መ. ንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤

2 በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን። (ሮሜ 5፡1-2)። የሰይጣን መንግሥት አባል የሆኑ ሰዎች ከገቡ በኋላ መልሰው ፈጽሞ ሊተዉት ይችላሉ?

ሠ. ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ። (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4)። ለምንድን ነው ሁሉም ከሰይጣን መንግሥት አያመልጡም?

ረ. ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ። (ራዕይ 20፡10)። የሰይጣን መንግሥት የሚጠፋው መቼ ነው?

2. የእግዚአብሔርን የጸጋ መንግሥት አስቡ፡-

ሀ. "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና።" (ሮሜ 14፡17)። ፈሪሳውያንም። የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ብለው ቢጠይቁት፥ መልሶ። የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም ደግሞም። እንኂት በዚህ ወይም። እንኂት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው። (ሉቃስ 17፡ 20-21)። የጸጋው መንግሥት የሚገኘው የት ነው?

ለ. ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና። (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡25)። በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት። የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው። (ራዕይ 19፡16) የጸጋውን መንግሥት የሚገዛው ማን ነው?

ሐ. "[አብ] ከጨለማ ሥልጣን አዳነን ወደ ሚወደው የወልድ [የጸጋ መንግሥት] መንግሥት አገባን" (ቆላስይስ 1:13) አንድ ሰው ከገዥዎች አንዱ በመሆን ወደ ጸጋው መንግሥት እንዴት ይገባል?

መ. መ. "ከሰጠኝ ሁሉ አንድ ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ [ኢየሱስ] የላከኝ [የተገለጠው] ፈቃድ ይህ ነው" (ዮሐ 6፡39)። “ያመንሁትን አውቃለሁ፥ የሰጠሁትንም አደራ በዚያ ቀን ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቻለሁ” (2ጢሞ. 1፡12)። ወደ ጸጋው መንግሥት የሚገቡት ወደ ሰይጣን መንግሥት ሊመለሱ ይችላሉን?

3. የእግዚአብሔርን የወደፊት የክብር መንግሥት አስብ፡-

3. የእግዚአብሔርን የወደፊት የክብር መንግሥት አስብ፡-

ሀ. ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን። (2ኛ ጴጥሮስ 3፡13) የክብር መንግሥት ምንድን ነው?

ለ. ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው። (ሮሜ 8፡30)። አንድ ሰው ወደ ከበአው መንግሥቱ እንዴት ይገባል?

ሐ. ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል። (ኢሳ 9: 7). እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤

33 በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም። (ሉቃስ 1፡32-33)። የክብር መንግሥት እስከ መቼ ነው የሚቆየው?

4. ጀምስ ፊሸር በአጭሩ ካቴኪዝም ጸጋ እና ክብርን በአንድ መንግስታት እንዳሉ ሁለት የአንድ መንግስት ግዛቶች አድርጎ ይመለከታቸዋል፡ “ፀጋ የክብር መጀመሪያ ነው፣ ክብር ደግሞ ፀጋን የተሟላ የሚያደርግ ነው በማለት አብራርቷል። ይህ የእሱ አባባል ምን ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

5. የሚከተሉት ምንባቦች በዋነኝነት የሚያመለክቱት የትኞቹን መንግሥታት ነው?

ሀ.ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ። (ቆላስይስ 3፡4)።

ለ.ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት፡፡ እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት፡፡ ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡ (1ዮሐ. 1፡5-7)፡፡

ሐ. ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡ ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡ (1ዮሐ. 2፡15-17)፡፡

መ. ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፥ ፀሐይም ትኵሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም፤ በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል፡፡ (ራዕይ 7፡15-17)፡፡

ሠ. ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ። (ራዕይ 22፡5)።

ረ. አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና። (ራዕይ 22፡20)

6. "ዓይኖቻቸውን ክፈት ከጨለማ ወደ ብርሃን መልስ" (ሐዋ. 26፡18)። በሐዋርያት ሥራ 9፣ ላይ አካላዊ እና መንፈሳዊ እይታው የተቀበለ ማን ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ

1. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ “የእግዚአብሔር ፈቃድ” የሚያሳየው የእርሱን_____ ወይም_____ነው።

2. _____ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም _____ነው። (ዘዳ.29፡29)።

3. የእግዚአብሔር ስውር ፈቃድ ምንድን ነው?

4. የእግዚአብሔር የተገለጠው ፈቃድ ምንድን ነው?

5. እግዚአብሔር በዮሴፍ ሕይወት ውስጥ ምን ዓይነት ድብቅ ፈቃድ አደረገ?

6. ዮሴፍ የእግዚአብሔርን የተገለጠ ፈቃድ የተከተለው በየትኞቹ መንገዶች ነው?

7. “የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ቢሆን፥ ክፉ ስለ ማድረግ ሳይሆን በጎ ስለ ማድረግ መከራን ብትቀበሉ ይሻላችኋልና።” (1ኛ ጴጥሮስ 3፡17)። የእግዚአብሔር ፈቃድ አንዳንድ ጊዜ ምንድን ነገሮችን ያካትታል?

8. “የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” (ሮሜ 12፡2)። ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚገልጸው እንዴት ነው፣ ደግሞስ ይህ ጥቅስ ስለ ራስህ ፈቃድ ምን ሊያመለክት ይችላል ብለህ ታስባለህ?

ክፍል IX: የጌታ ጸሎት

ምዕራፍ 3፡ የእግዚአብሔር አቅርቦት እና ምሕረት

ካቴኪዝም

ጥ. በአራተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. በአራተኛው ልመና፣ ማለትም፣ *የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን* በሚለው ከእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ በቂ የሆኑ የህይወት መልካም ነገሮች እንድንቀበልና ከእነሱ ጋር በእርሱ በረከት እንድንደሰት እንጸልያለን።

ጥ. በአምስተኛው ልመና ውስጥ ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. በአምስተኛው ልመና፣ ማለትም *የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን፣* በሚለው እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ሲል ኃጢአታችንን በነፃ ይቅር እንዲለን እንጸልያለን። በጸጋው ሌሎችን ይቅር ለማለት ከልባችን ስለ ቻልን ልንለምነው የምንበረታታ እንሆናለን።

<u>ቃላትን አብራራ</u>

መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ታዳጊዎች ከታች የተዘረዘሩትን ቃላት ትርጉም እንዲፈልጉ ጠይቃቸው፡ የእያንዳንዱን ፍች እንዲያነቡና ከዚያም የተጻፈውን ፍቺ ሳያዩ ቃሉን በራሳቸው አባባል ለመተርጎም ይሞክሩ። እያንዳንዱን ቃል በደንብ እስኪረዱት ድረስ ትርጉሙን በማንበብ እና በራሳቸው አባባል በየተራ እንዲገልጹ ንገራቸው። የተጻፈውን ፍች በእያንዳንዱ ጊዜ በቀላሉ የሚደጋግሙ ከሆነ በመጀመሪያ የሁሉንም ቃላት ፍችዎች እንዲያነቡ ምራቸው፤ ከዚያም ሳያዩ የሁሉንም ቃላት ፍች በራሳቸው አባባል ይግለጹ። በመቀጠል የካቴኪዝም ጥያቄዎችን እና መልሶችን እንደገና አንብበው ስለ አራተኛው እና አምስተኛው ልመናዎች በተቻላቸው መጠን በራሳቸው አባባል ያብራሩ።

ብቃት ያለው

እዳዎች

ተበዳሪዎች

ይቅርታ

<u>በቀላል መንገድ እንደገና መፃፍ</u>

በተሻለ ግንዛቤ ላይ በመመስረት ካቴኪዝምን በራሳችሁ አባባል ፃፉ።

ጥ.

መ.

ጥ.

መ.

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ</u>

እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚደግፈውን የካቴኪዝም ሐረግ(ዎች) ለዩ።

መዝሙረ ዳዊት 51:1 አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ።

መዝሙረ ዳዊት 90:17 የአምላካችን የእግዚአብሔር ብርሃን በላያችን ይሁን። የእጆቻችንንም ሥራ በላያችን አቅና።

ምሳሌ 30፡8-9 ከንቱነትንና ሐሰተኛነትን ከእኔ አርቃቸው፤ ድኅነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ፤ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ፥ እንዳልጠግብ እንዳልክድህም። እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፤ ድሀም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም፥ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል።

ዳንኤል 9:18–19 አምላኬ ሆይ፥ በፊትህ የምንለምን ስለ ብዙ ምሕረትህ ነው እንጂ ስለ ጽድቃችን አይደለምና ጆሮህን አዘንብለህ ስማ፤ ዓይንህን ገልጠህ ጥፋታችንና ስምህ የተጠራባትን ከተማ ተመልከት።

19 ፤ አቤቱ፥ ስማ፤ አቤቱ፥ ይቅር በል፤ አቤቱ፥ አድምጥና አድርግ፤ አምላኬ ሆይ፥ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና ስለ ራስህ አትዘግይ።

ማቴዎስ 6፡14 ንጉሡም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ በጣም አዘነ፥ ያድነውም ዘንድ ልቡን ወደ ዳንኤል አደረገ፤ ሊያድነውም ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ደከመ።

ሮሜ 3፡24 “[አማኞች] በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ቤዛነት በሉል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።

ኤፌሶን 1:7፣ በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።

<u>የካቴኪዝም ጥያቄዎች</u>

1. ኢየሱስ እንድንጸልይ የተናገረው “የዕለት እንጀራ” ምንድን ነው?

2. ለዕለት እንጀራ መጸለይ በእርግጥ አስፈላጊ ነውን ወይስ ሁሉም ሰው ያለው መብት ብቻ ነው?

3. አምስተኛው ልመና የሚያመለክታቸው “ዕዳዎች” ምንድን ናቸው?

4. አምስተኛው ልመና የሚያመለክታቸው “ባለዕዳዎች” እነማን ናቸው?

5. እግዚአብሄር ይቅር እንዲልህ መጸለይ ያለብህ በምን መሠረት ላይ ነው?

6. ክርስቲያኖች ሌሎችን ከልባቸው ይቅር እንዲሉ የሚረዳቸው ምንድን ነው?

7. ክርስቲያኖች ኃጢአት ሲሠሩ የእግዚአብሄርን ይቅርታ እንዲፈልጉ የሚያበረታታቸው ነገር ምንድን ነው?

<u>የቃል ጥቅስ</u>

ፊልጵስዩስ 4፡19 “አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባቹሀል።”

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች አምላክ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እንደሚያሟላላቸው ነግሩዋቸዋል? "የሚያስልጓቸው ነገሮች ምንድን ናቸው"?

2. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን” ብለው እንዲጸልዩ አዘዛቸው። "የዕለት እንጀራ" ምንድን ነው?

3. የአሸሊ ዳውን የህጻናት ማሳደጊያ ዕለታዊ ፍላጎቶችን በማሟላት ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን ታማኝ ሆኖ ያገኘው ማነው?

4. ከንቱነትንና ሐሰተኛነትን ከእኔ አርቃቸው፤ ድኅነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ፤ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ፥ እንዳልጠግብ እንዳልክድህም። እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፤ ድሀም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም፥ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል። (ምሳሌ 30፡8-9)። በራስህ አባባል ይህ ጥቅስ ምን ለማለት ፈልጎ ነው ብለህ ታስባለህ?

5. ባለጠጎች ደኸዩ፥ ተራቡም፥ እግዚአብሔርን የሚፈልጉትን ግን ከመልካም ነገር ሁሉ አይጐድሉም። (መዝ. 34፡10)። እግዚአብሔር አምላክ ምሕረትንና እውነትን ስለ ወደደ፥ ሞገስንና ክብርን ይሰጣል፤ እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም። (መዝ. 84፡11)። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል። (ማቴዎስ 6:33-34) እነዚህ ሦስቱ ጥቅሶች የሁሉንም ፍላጎት ለማሟላት ምን ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ?

6. ዓመፃን ተስፋ አታድርጉ፥ ቅሚያንም አትተማመኑት፤ ባለጠግነት ቢበዛ ልባችሁ አይኩራ። (መዝ. 62፡10)። "በአሁኑ ዓለም ባለ ጠጎች የሆኑት እንዳይታበዩ ወይም በማይታመን ባለጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው ነገር ግን ደስ የሚያሰኘውን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በእግዚአብሔር ተስፋ እንዲያደርጉ እዘዛቸው" (1ጢሞ. 17) ሀብታም መሆን ኃጢአት ነው?

7. እግዚአብሔርም ሙሴን። በሕጌ ይሄዱ ወይም አይሄዱ እንደሆነ እኔ እንድፈትናቸው፥ እነሆ ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ፤ ሕዝቡም ወጥተው ለዕለት ለዕለት የሚበቃቸውን ይልቀሙ። እንዲህም ይሆናል፤ በስድስተኛው ቀን ያመጡትን ያዘጋጁ፥ ዕለት ዕለትም ከሚለቅሙት ይልቅ ሁለት እጥፍ ይሁን አለው። (ዘጸአት 16፡4-5)። ይህ ክፍል ከአራተኛው ልመና ጋር እንዴት ይዛመዳል ብልህ ታስባለህ?

8. ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? (ማቴዎስ 6:26) በዚህ ጥቅስ ውስጥ ከትንሽ እስከ ትልቅ ድረስ የሚከራከሩበት ነገር ምንድነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፡- ሌሎችን ይቅር ማለት

1. "የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን" በዚህ አምስተኛ ልመና “በደላችን” እና “የበደሉን” ሲል ምን ማለት ነው?

2. ሌሎችን ይቅር ለማለት ከትልቅ እስከ ትንሽ የሚከራከሩበት ምንድን ነው?

3. "*መሳሳት* ሰብዓኢ ነው፥ ይቅር ለማለት ደግሞ *መ*ለኮታዊ ነው" (አሌክሳንደር ጳጳስ). በአጭር ካቴኪዝም #105 *መ*ሰረት፣ አማኞች ሌሎችን ይቅር እንዲሉ የሚያስችላቸው ነገር ምንድን ነው?

4. "ይቅርታ ማለት እኔን በመጉዳትህ አንተን ለመጉዳት የነበረኝን መብቴን መተው ነው" ይህ የይቅርታ ትርጉም ምን ነገር ይጎድለዋል?

5. አንድን ሰው በእውነት ይቅር አልከው፤ ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ ስለ ጥፋቱ ማሰብ ጀምረህ ከተናደድክ ምን ማድረግ አለብህ?

6. የተደረገብህን በደል ሳትረሳው በእውነት ይቅር ማለት ትችላለህ?

7. በዘፍጥረት 50፡17-21 ሌሎችን እንዴት ይቅር ማለት እንደሚቻል ያሳየው ማን ነው?

8. በሐዋርያት ሥራ 7፡54-60 *መሠረት* ምንም እንኳን በዳዮቻቸው ይቅርታ ለመጠየቅ ባይፈልጉም ክርስቲያኖች የበደሏቸውን ሰዎች ይቅር ማለት አለባቸው?

9. በማቴዎስ 18:21-22 *መሠረት* ክርስቲያኖች የሚበድሏቸውን ሰዎች ምን ያህል ጊዜ ይቅር ማለት አለባቸው?

10. አንድ ሰው ብዙ ጊዜ ዋሽቶሀል ወይም ሰርቆሀል። በዚህም እምነትህን ደጋግሞ በድሏል እንበል። በእያንዳንዱ ጊዜ በእውነት ይቅር ብለኸው ከሆነ ወደፊት እሱን ልታምነው እና እንደዳልዋሸች ወይም እንዳልሰረቀች አድርገህ መያዝ ይኖርብሃልን?

ክፍል IX: የጌታ ጸሎት

ምዕራፍ 4፡ የእግዚአብሔር ማዳን እና የበላይነት

ካቴኪዝም

ጥ. በስድስተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?

መ. በስድስተኛው ልመና *"ወደ ፈተና አታግባን፣ ከክፉ አድነን እንጂ"* በሚለው እግዚአብሔር በኃጢአት ከመፈተን እንዲጠብቀን፣ ወይም ስንፈተን እንዲደግፈን እና እንዲያድነን እንጸልያለን።

ጥ. የጌታ ጸሎት መደምደሚያ ምን ያስተምረናል?

መ. የጌታ ጸሎት መደምደሚያ፣ *"መንግሥት ያንተ ናትና፣ ኃይል፣ ክብር፣ ምስጋና ለዘላለም አሜን።"* የሚለው ማበረታቻ ከእግዚአብሔር ብቻ እንድንቀበል ያስተምረናል፣ በጸሎታችንም ውዳሴን፣ መንግሥትን፣ ኃይልን እና ክብርን ለእርሱ እንሰጠዋለን። ምኞታችን መሆኑንና መስማማታችንን ለማአጋገጥ አሜን እንላለን።

<u>ቃላትን አብራሩ</u>

መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ታዳጊዎች ከታች የተዘረዘሩትን ቃላት ትርጉም እንዲፈልጉ ጠይቃቸው፡ የእያንዳንዱን ፍች እንዲያነቡና ከዚያም የተጻፈውን ፍቺ ሳያዩ ቃሉን በራሳቸው አባባል ለመተርጎም ይሞክሩ። እያንዳንዱን ቃል በደንብ እስኪረዱት ድረስ ትርጉሙን በማንበብ እና በራሳቸው አባባል በየተራ እንዲገልጹ ንገራቸው። የተጻፈውን ፍች በእያንዳንዱ ጊዜ በቀላሉ የሚደጋግሙ ከሆነ በመጀመሪያ የሁሉንም ቃላት ፍችዎች እንዲያነቡ ምራቸው፤ ከዚያም ሳያዩ የሁሉንም ቃላት ፍች በራሳቸው አባባል ይግለጹ። በመቀጠል፣ የካቴኪዝም ጥያቄዎችን እና መልሶችን እንደገና ያንብቡ እና ስለ ስድስተኛው ልመና እና የጌታ ጸሎት መደምደሚያ በተቻለ መጠን በራሳቸው አባባል ያብራሩ።

ፈተና

መንግሥት

ክብር

ኣሜን

ምስክርነት

<u>በቀላል መንገድ እንደገና መፃፍ</u>

በቃላቱ አገባብ ላይ በተሻለ ግንዛቤ ላይ በመመስረት ካቴኪዝምን በራሳችሁ ቃላት እንደገና ፃፉ

ጥ.

መ.

ጥ.

መ.

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ</u>

እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚደግፈውን የካቴኪዝም ሐረግ(ጎች) ለዩ።

1ኛ ዜና 29:11፣ አቤቱ፥ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል፥ ክብርም፥ ድልና ግርማ ለአንተ ነው፤ አቤቱ፥ መንግሥት የአንተ ነው፥ አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ።

መዝሙረ ዳዊት 10:17 "እግዚአብሔር የድሆችን ምኞት ሰማ፥ ጆሮውም የልባቸውን አሳብ አደመጠች፥

መዝሙር 19፡13 የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ፤ የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ፥ ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ።

መዝሙረ ዳዊት 77:1 በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥ ቃሌም ወደ እግዚአብሔር ነው፥ እርሱም አደመጠኝ።

ሚክያስ 7፡7 እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እመለከታለሁ፥ የመድኃኒቴንም አምላክ ተስፋ አደርጋለሁ፤ አምላኬም ይሰማኛል።

ማቴዎስ 26፡41 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።

1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5፡14-15 በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።

የካቴኪዝም ጥያቄዎች

1. **የጌታ ጸሎት መሠረታዊ ክፍሎች ምንና ምን ናቸው?**

2. **ስድስተኛው ልመና እንድትጸልዩ የሚነግራችሁ ስለ ምን ሁለት ነገሮች ነው?**

3. **በጌታ ጸሎት ማጠቃለያ ላይ ጌታን የምናሳስበው ሶስት ነገሮች ምንድናቸው?**

4. **እነዚህን ሦስት ነገሮች ለእግዚአብሔር ስትነግረው ምን ታደርጋለህ?**

5. በምትጸልዩበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ ያላችሁን ፍላጎት እና እምነት የሚገልጸው የትኛው ቃል ነው፤ እና ይህ ቃል ምን ይገልጻል?

የቃል ጥቅስ

1ኛ ቆሮንቶስ 10፡13 “በሰው ዘንድ ካለው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም። እግዚአብሔርም የታመነ ነው; ከምትሸከሙት በላይ እንድትፈተኑ አይፈቅድም። ስትፈተኑ ግን ከሥሩ እንድትቀሙ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።”

1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሰው የትኞቹን ሦስት የፈተና ምንጮች ነው?

2. “ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ። እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?” (ሮሜ 7፡23-24) ‘ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።” (ገላትያ 5፡17) በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የትኛው ሐዋርያ ነው ስለ አሮጌው ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ድካም እና ለፈተና መጋለጥ የተናገረው?

3. ለፈተና በየትኞቹ አማራጮች ምላሽ መስጠት ትችላለህ?

4. የተፈተነ ነገር ግን ኃጢአት ያልሠራ ማን ነው?

5. አንድ ጓደኛዋ ሰይጣን በፈተናት ቁጥር ንስሃ እንደምትገባ ትናገራለች። ምላሽህን ከጠየቀች ምን ልትላት ትችላለህ።

6. ፈተናዎች በየትኞቹ መንገዶች የተለመዱት ሊሆኑ ይችላሉ?

7. ፈተናንና ውጤቱን እንድትቋቋም የሚረዳህ እግዚአብሄር ምን ያህል ታማኝ ነው?

8. “ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ። እኔ ግን ስለ አንተ ጸለይኩ... እምነትህ እንዳይጠፋ። በተመለስህ ጊዜም ወንድሞችህን አጽና” (ሉቃስ 22፡31-32)። ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ስለሚመጣው ፈተና ያስጠነቀቀው የትኛውን ሐዋርያ ነው?

9. በዘፍጥረት 39፡10 ዮሴፍ ከፈተና እንዴት አመለጠ?

10. በሚከተሉት ጥቅሶች በመመሥረት ፈተና ሲያጋጥምህ መቋቋም እንድትችል መንፈሳዊ ጥንካሬህን ለመጨመር ምን ልታደርግ ትችላለህ?

ሀ. "አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ" (መዝሙረ ዳዊት 119:11)

ለ.."እኔ ግን እግሮቼ ሊሰናከሉ፥ አረማመዴም ሊወድቅ ትንሽ ቀረ።
የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና።" (መዝ. 73፡2-3)።

ሐ. "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም
በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤
የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ" እጸልያለሁ (ኤፌሶን 3፡16)

መ. "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ። ዲያብሎስን ተቃወሙት ከእናንተም
ይሸሻል" (ያዕቆብ 4፡7)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፡ እግዚአብሔርን ከፍ ማድረግ

1. የጌታ ጸሎት መደምደሚያ ምን ሦስት ነገሮችን ያስተምራል?

2. በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ኤልያስ የበኣል ነቢያት ያላደረጉትን ምን ነገር አደረገ?

3. የጌታ ጸሎት በምንጸልይበት ጊዜ ስለእግዚአብሔር ማንነት እንድንናገር የሚያስተምረን የትኞቹን ሦስት ነገሮች ነው?

4. የእግዚአብሔር መንግሥት ከጸሎት ጋር ምን ያገናኘዋል?

5. የእግዚአብሔር ኃይል ከጸሎት ጋር ምን የገናኘዋል?

6. የእግዚአብሔር ክብር ከጸሎት ጋር ምን ያገናኘዋል?

7. ንጉስ ዳዊት፡ “አቤቱ፥ የአባታችን የእስራኤል አምላክ ሆይ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ተባረክ። አቤቱ፥ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል፥ ክብርም፥ ድልና ግርማ ለአንተ ነው፤ አቤቱ፥ መንግሥት የአንተ ነው፥ አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ። ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው፥ አንተም ሁሉን ትገዛለህ፤ ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው፤ ታላቅ ለማድረግ፥ ለሁሉም ኃይልን ለመስጠት በእጅህ ነው። አሁንም እንግዲህ፥ አምላካችን ሆይ፥ እንገዛልሃለን፥ ለክቡር ስምህም ምስጋና እናቀርባለን።” አለ። (1ኛ ዜና 29፡10-13)። የጌታ ጸሎት መደምደሚያ የእግዚአብሔርን መንግሥት፣ ኃይል እና ክብር ይመሰክራል። ዳዊት በጸሎቱ ያወሳው ከእነዚህ ከሦስቱ ነገሮች መካከል የትኛውን ነው?

8. ልመናን በተመለከተ “አሜን” ማለት ምን ማለት ነው?

9. **ውዳሴን በተመለከተ “አሜን” ማለት ምን ማለት ነው?**